# የወንጀል ቅጣትን መገደብ፡- በኢትዮጵያ ያለው የሕግ ማዕቀፍና አፈጻጸሙ በአማራ ክልል

*በላይነህ አድማሱ* ዓለሙ ዳኛው**

## *አህጽሮተ ፅሁፍ*

*ለወንጀል ቅጣት ውሳኔ ጊዜ መስጠትና የቅጣቱን መጠን ወስኖ አፈጻጸሙን በመገደብ የወንጀለኛውን አመል መፈተን በወንጀል ፍትህ ሥርዓት ውስጥ ተግባራዊ የሚደረግ አሰራር ነው። በወንጀል ክርክር ጥፋተኝነትንና ቅጣትን ወስኖ እንዲፈጸም ማድረግ መደበኛ አሰራር ቢሆንም ፍርደኛው ጥፋተኛነቱን እንዲያውቅ በማድረግ ቅጣቱን ማዘግየት ወይም የቅጣት መጠኑን ወስኖ አፈጻጸሙን ማገድ ለባሕርይው መስተካከል ተገቢ እንደሆነ ሲታመንበት ይሄው ሊወሰን እንደሚችል የኢፌዴሪ የወንጀል ሕግ ያሳያል። ይሁን እንጅ ለወንጀል ቅጣት ውሳኔ ጊዜ የሚሰጠውም ይሁን የቅጣት መጠኑ ተወስኖ አፈጻጸሙ የሚታገደው በሕጉ የተመለከቱት መስፈርቶች ተሟልተው ሲገኙ ነው። በአማራ ክልል ፍርድ ቤቶች ለቅጣት ውሳኔ ጊዜ መስጠት የማይተገበር ቢሆንም የቅጣት መጠኑን ወስኖ የፈተና ጊዜ በመስጠት አፈጻጸሙን መገደብ የተለመደ አሰራር ነው። ከዚህ ጋር ተያይዞ በክልሉ ፍርድቤቶች የወንጀል ቅጣትን በመገደብ ረገድ የሚስተዋሉ ችግሮች ያሉ ሲሆን የዚህ ጥናት ዓላማም ችግሮቹን በመለየት የመፍትሄ ሃሳብ ማመንጨት ነው። የጥናቱን ዓላማ ለማሳካትም አይነታዊ የጥናት ዘዴ ተግባራዊ ሆኗል። በጥናቱም ለወንጀል ቅጣት ውሳኔ ጊዜ መስጠትን አስመልክቶ በቂ ግንዛቤ እንደሌለና ተግባራዊ እንደማይደረግ፣ የወንጀል ቅጣትን ወስኖ አፈጻጸሙን መገደብ የተለመደ ቢሆንም የወንጀሉ ክብደት፣ የቅጣቱ መጠንና የወንጀለኛው ባሕርይ ግምት ውስጥ ሳይገባ በሕጉ የተመለከተው ዝቅተኛው የፈተና ጊዜ (ሁለት ዓመት) እንደሚሰጥ፣ በፍርዱ የጠባይ አመራር ደንብ አለመገለጹ፣ ይህንኑ የሚያስፈጽም ተቋም ማቋቋም እንደሚገባ ሕጉ የደነገገ ከመሆኑም ባሻገር በተግባር የሚስተዋለው ችግር የተቋሙን አስፈላጊነት የሚያሳይ ቢሆንም ይሄው አለመፈጸሙ፣ ገደቡ መልካም ፍሬ ማስገኘቱን አለመረዳት፣ የገደብ ውሳኔው በሚሻርበት ጊዜ የሚኖረው የክርክር ሥነ-ሥርዓት ምን ሊሆን እንደሚገባ በሕጉ በግልጽ አለመመልከቱ፤ የሚሉት ግኝቶች ተለይተው ለእያንዳንዳቸው የመፍትሄ ሃሳብ ቀርቧል።*

***ቁልፍ ቃላት፡-*** የወንጀል ቅጣት፣ ገደብ፣ ለወንጀል ቅጣት ውሳኔ ጊዜ መስጠት፣ የወንጀል ቅጣት እንዳይፈጸም ማገድ፣ የፈተና ጊዜ፣ የጠባይ አመራር ደንብ

## *መግቢያ*

የወንጀል ቅጣት ገደብ ለቅጣት ውሳኔ ጊዜ መስጠትንና ቅጣትን ወስኖ አፈጻጸሙን ማገድን የሚያካትት ነው።[1] በወንጀል ክርክር ሂደት ጥፋተኝነትንና ቅጣትን ወስኖ ውሳኔውን

---

* በሕግ የመጀመሪያ ዲግሪ (አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ)፣ ሁለተኛ ዲግሪ በወንጀል ሕግ (አምስተርዳም ዩኒቨርሲቲ)፣ ረዳት ፕሮፌሰር፣ ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ሕግ ትምህርት ቤት፡ badmaasu7@gmail.com ወይም belaynehv@yahoo.com

* በሕግ የመጀመሪያ ዲግሪ (ጅማ ዩኒቨርሲቲ)፣ ሁለተኛ ዲግሪ በወንጀል ፍትህ አስተዳደር እና ሰብአዊ መብት ሕግ (ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ)፣ ረዳት ፕሮፌሰር፣ ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ሕግ ትምህርት ቤት፡ alemudag@gmail.com
ለምርምሩ መሳካት እና ህትመት መብቃት አስፈላጊውን መረጃ በመስጠት እና ጽሁፉን በመገምገም አስተዋጽኦ ላበረከቱልን ባለሙያዎች የላቀ ምስጋናችን ይድረሳቸው።

እንዲፈጸም ማድረግ መደበኛ አሰራር ነው፡፡ ይሁን እንጅ የወንጀለኛው ጥፋተኝነት ተወስኖ በገደብ ቢለቀቀ የባሕርይ መሻሻል ሊያመጣ ይችላል ተብሎ ሲታመን ለቅጣት ውሳኔ ጊዜ ሊሰጥ ይችላል፡፡[2] ይህ የሚደረገውም የፈተና ጊዜ ተቆርጦለት ነው፡፡[3] በዚህ የፈተና ጊዜ ቅጣቱ ሳይወሰንበት በፈተና ሆኖ አመሉ እንዲፈተሽ የተደረገው ጥፋተኛ የሚያከብራቸው ግዴታዎች በፍርዱ ይመለከታሉ፡፡[4] እነዚህን ግዴታዎች ማክበርና አለማክበሩ ለባሕርይው መሻሻል ወይም አለመሻሻል ማሳያ ይሆናሉ፡፡ ይህ አይነቱ ገደብ በኢፌዴሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 191 ላይ በግልጽ ተደንግጎ ይገኛል፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሠረት ክስ የቀረበበት ወንጀለኛ ጥፋተኛ እንደሆነ ተወስኖ ቅጣቱ ሳይወሰን እንዲዘገይ በማደረግ ወንጀለኛው ከጥፋቱ እንዲማር ይደረጋል፡፡

በጥፋተኛው ላይ ቅጣት ወስኖ አፈጻጸሙን መገደብ በፍትህ ሥርዓቱ ውስጥ ያለ ሌላው የገደብ አይነት ነው፡፡[5] በወንጀል ተከስሶ ጥፋተኛ እንደሆነ የተወሰነበት ሰው አንድ ጽኑ ማስጠንቀቂያ ቢሰጠው ባሕርይውን የሚያሻሽልና ወደፊት ሌላ ወንጀል ከመፈጸም የሚቆጠብ መሆኑ የታመነበት እንደሆነ ቅጣት ተወስኖ እንዲያውቀው ከተደረገ በኋላ ይሄው እንዳይፈጸም ሊታገድ ይችላል፡፡[6] የወንጀል ቅጣቱ አፈጻጸም የሚታገደው የወንጀለኛውን ባሕርይ ለመፈተን የሚያስችል በሕጉ የተመለከተውን የፈተና ጊዜ በመስጠትና በዚሁ ጊዜ ወንጀለኛው ሊያከብራቸው የሚገቡ የጠባይ አመራር ደንቦችን በፍርዱ ላይ በመግለጽ ነው፡፡[7] የወንጀል ቅጣት አፈጻጸሙ የታገደለት ፍርደኛ የተወሰነበትን ቅጣት በማረሚያቤት ውስጥ ሆኖ ከመፈጸም ይልቅ ከማህበረሰቡ ጋር ተቀላቅሎ በፈተና ጊዜው መልካም ባሕርይን እያሳየ ለሕግና ለተጣሉበት ግዴታዎች ተገዥ መሆኑን እንዲያረጋግጥ ይጠበቅበታል፡፡[8]

ለወንጀሉ ቅጣት ውሳኔ ጊዜ በመሰጠቱ ወይም ቅጣቱ ተወስኖ አፈጻጸሙ በመታገዱ በፈተና ጊዜ እንዲቆይ የተደረገው ጥፋተኛው በተሰጠው የፈተና ጊዜ ውስጥ የባሕርይ መሻሻል ማሳየቱንና ገደቡ መልካም ፍሬ ማስገኘቱን ለማረጋገጥ የገደቡን አፈጻጸም መከታተል ያሻል፡፡ በዚህም መሠረት በፈተና እንዲቆይ የተደረገውን ወንጀለኛ በፍርዱ የተገለጸለትን የጠባይ አመራር ደንብ ማክበሩንና መልካም ዜጋ መሆኑን የሚከታተል ተቆጣጣሪ ሊኖር እንደሚችል በኢፌዴሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 199 ላይ ተመልክቷል፡፡ በዚህ መሠረት ተቆጣጣሪው በፈተና ጊዜ ሆኖ አመሉ እንዲፈተሽ የተወሰነበትን ሰው አኗኗር ሁኔታ የመከታተልና ጠባዩ የሚታረምበትን መንገድ የመምራት ኃላፊነት ይኖርበታል፡፡ ወንጀለኛው በፈተና ጊዜ ውስጥ እያለ በፍርዱ የተገለጹትን የጠባይ አመራር ደንብ ያላከበረ ወይም አዲስ ወንጀል የፈጸመ እንደሆነ በፍርድ ቤቱ ልዩ ልዩ እርምጃዎች ሊወሰዱ ይችላሉ፡፡[9] ወንጀለኛው የጠባይ አመራር ደንቦችን ከጣሰ እንደነገሩ ሁኔታ ማስጠንቀቂያ ሊሰጠው፣ አዲስ የጠባይ አመራር

---

[1] 'Suspended Sentence', west's Encyclopedia of America, retrived from https://www.encyclopedia.com, last accessed 13 September 2019

[2] የኢፌዴሪ የወንጀል ሕግ፣ አዋጅ ቁጥር 414/1997፣ ነጋሪት ጋዜጣ፣1997፣ አንቀጽ 190 እና ተከታዮቹ (ከዚህ በኋላ የኢፌዴሪ የወንጀል ሕግ፤ ተብሎ ይገለጻል)፡፡

[3] ዝኒከማሁ፣ አንቀጽ 191 እና 196 በጣምራ ይመለከቷል፡፡

[4] ዝኒከማሁ፣ አንቀጽ 198፡፡

[5] Dejene Girma Janka, *A Hand Book on the Criminal Code of Ethiopia,* 2013, pp. 185-186

[6] የኢፌዴሪ የወንጀል ሕግ፣ በግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 2 ላይ እንደተገለጸው፣ አንቀጽ 192፡፡

[7] ዝኒከማሁ፣ አንቀጽ 198፡፡

[8] Hussey, Frederic A. Duffee & David E., *probation, parole and community Field Service: policy, Structure and process* (Harper and Row publishers, Neyork, 1980) p. 35 በተጨማሪም የኢፌዴሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 200 ተቃራኒ ንባብን ይመለከቷል፡፡

[9] ፀሐይ ወዳ፣ *የወንጀል ሕግ መሠረታዊ መርሆዎች* (ጥር 19 ቀን 1994) ገጽ 228፡፡

ደንብ ሊወሰንበት፣ የፈተና ጊዜው ሊራዘምና ገደቡ ተሽሮ አዲስ ቅጣት ሊወሰንበት ወይም ቀደም ሲል የተወሰነውን ቅጣት እንዲፈጽም ሊታዘዝ እንደሚችል የወንጀል ሕጉ በአንቀጽ 200 ደንግጓል፡፡

በኢፌዴሪ የወንጀል ሕግ ለቅጣት ውሳኔ ጊዜ መስጠትና ቅጣትን ወስኖ አፈጻጸሙን መገደብ በግልጽ ይደንገጉ እንጅ የሕግ አተረጓጎምና አፈጻጸም ችግሮች በተግባር ይስተዋላሉ፡፡ የዚህ ጥናት ዋና ዓላማም ችግሮችን በመለየት የመፍትሄ ሃሳቦችን አመንጭቶ የፍትህ ሥርዓቱን ለማሻሻል የሚያግዝ አስተዋጽኦ ማድረግ ነው፡፡ በዚህ መሠረት የሚከተሉትን ለጥናቱ መነሻ የሆኑ ጥያቄዎች በማንሳት ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ ለመመለስ ጥረት ተደርጓል፡፡ የተነሱት ዋና ዋና ጥያቄዎችም ለወንጀል ቅጣት ውሳኔ ጊዜ መስጠትና ቅጣቱን ወስኖ አፈጻጸሙን መገደብን በተመለከተ የሚስተዋሉ የሕግ ክፍተቶችና ግልጽነት አሉን? ለወንጀል ቅጣት ውሳኔ ጊዜ መስጠት በአማራ ክልል ፍርድቤ ቶች አፈጻጸሙ ምን ይመስላል? የወንጀል ቅጣትን ወስኖ አፈጻጸሙን ማገድ በእነዚሁ ፍርድቤቶች እንዴት ተግባራዊ ይደረጋል? በሁለቱም የገደብ አይነቶች የፈተና ጊዜና የጠባይ አመራር ደንቦች አሰጣጥ ምን ይመስላል? የፈተና ጊዜና የጠባይ አመራር ደንብ አፈጻጸም ክትትልና ቁጥጥር ሂደቱስ? በፈተና ጊዜ የሚሰጡ የጠባይ አመራር ደንቦች ሲጣሱ በአማራ ክልል ፍርድቤ ቶች የሚወሰድ እርምጃ ምን ይመስላል? የገደብ ውሳኔ ሲሻር የፍርደኛው የመደመጥ መብት እንዴት ተግባራዊ ይሆናል? የሚሉ ናቸው፡፡

ጥያቄዎቹን ለመመለስ አይነታዊ የጥናት ዘዴ ተግባራዊ የሆነ ሲሆን መረጃዎቹም በቃለ-መጠይቅ፣ በቡድን ተኮር ውይይትና በአማራ ክልል ፍርድ ቤቶች ከተሰጡ የገደብ ውሳኔዎች ናሙና በመውሰድ ተሰብስበው ከሕጉና በርእሰ ጉዳዩ ላይ ከተጻፉ መጣጥፎች ጋር በመገናዘብ ተተንትነዋል፡፡

## 1. የወንጀል ቅጣትን የመገደብ ጽንሰ-ሃሳብ

"መገደብ"[10] እና "ማገድ"[11] የሚሉት ቃላት በኢ.ፌ.ዴ.ሪ የወንጀል ሕግ ውስጥ የወንጀል ቅጣትን በገደብ ማስቆምን አስመልክቶ በፍርድቤቶች ሊወሰን የሚችለውን ሁኔታ ለማመልከት ስራ ላይ ውለዋል፡፡ መገደብ ወይም ማገድ የወንጀል ጥፋተኝነትና ቅጣት ውሳኔ ተወስኖ ወዲያው ተግባራዊ በመሆን ፋንታ ጥፋተኛው በፈተና ሁኔታ ውስጥ ሆኖ ጠባዩ የሚፈተሽበትን አሰራር[12] የሚያሳይ ይሁን እንጅ ትርጉሙ በኢትዮጵያ ሕጎች ውስጥ በግልጽ አልተመለከተም፡፡ በመሆኑም የመገደብ ወይም የማገድን ጽንሰ-ሃሳብ- ከወንጀል ፍትህ አስተዳደር ሥርዓት አንጻር ለመገንዘብ አግባብነት ያላቸውን ጽሑፎች እንመለከታለን፡፡

ለወንጀል ቅጣት ውሳኔ ጊዜ መስጠትና የቅጣት ውሳኔ ለጊዜው እንዳይፈጸም የመገደብን ጽንሰ-ሃሳብ ለማብራራት መገደብ ለሚለው ቃል ትርጉም የሰጡ መዝገበ-ቃላትና ሌሎች የሕግ ሰነዶች የሚከተለውን ይላሉ፡፡ በብላክስ ሎው የሕግ መዝገበ-ቃላት መገደብ "ጥፋት ፈጽሞ የእስራት ቅጣት የተወሰነበት ሰው ቅጣቱን ለጊዜው እንዳይፈጽም የሚታገድበት የፍርድቤት ትእዛዝ ወይም ውሳኔ ሲሆን ይህ የሚደረገው ለፍርደኛው የፈተና ጊዜ

[10] የኢፌዴሪ የወንጀል ሕግ፣ በግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 2 ላይ እንደተገለጸው፣ ሁለተኛ መጽሐፍ፣ ርዕስ ሁለት፣ ምእራፍ አንድ፣ ክፍል ሁለት ይመልከቱ፡፡

[11] ዝኒከማሁ፣ አንቀጽ 192፡፡

[12] ዝኒከማሁ፣ አንቀጽ 191-199 ይመልከቷል፡፡

ተሰጥቶት በዚህ ጊዜ ውስጥ የጠባይ መሻሻል ያመጣና ሌላ ወንጀል ያልፈጸመ እንደሆነ ነው"[13] በሚል ተተርጉሞ ይገኛል፡፡ የመገደብ ጽንሰ-ሃሳብ በሌሎች ጽሑፎች ተመሳሳይ በሆነ መንገድ ተብራርቷል፡፡ በዚህም መሠረት የወንጀል ቅጣትን መገደብ ማለት ቅጣት ከተወሰነ በኋላ በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ እንዳይፈጸም በማገድ ፍርደኛው በማህበረሰቡ ውስጥ ሆኖ ባህሪውን እንዲያሻሽል የሚታዘዝበትና ክትትል የሚደረግበት ሥርዓት ነው፡፡[14] በአጭሩ የወንጀል ቅጣትን መገደብ ጥፋተኛው በፍርድቤት የተሰጠውን ትዕዛዝ እስካከበረ ድረስ የእስራት ፍርዱ እንዳይፈጸም ማገድ ነው፡፡[15]

ከላይ ከተመለከቱት ትርጓሜዎች መገንዘብ የሚቻለው የወንጀል ቅጣትን መገደብ ከወንጀል ቅጣት ውሳኔ ጋር ተያይዞ የሚፈጸም የወንጀል ፍትህ አስተዳደር ሥርዓቱ የተለመደ አሠራርና የሚከተሉትን ነጥቦች ያካተተ መሆኑን ነው፡፡ ፍርድ ቤት የሚሰጠው ውሳኔ ጥፋተኝነትንና ቅጣትን ሊይዝ የሚችል ሲሆን ገደብ ከነዚሁ ውሳኔዎች ጋር ተያይዞ ሊሰጥ ይችላል፡፡ በሌላ አነጋገር የጥፋተኝነት ወይም የቅጣት ውሳኔ መኖር ለገደብ ህልውና መሠረት ነው፡፡ የወንጀል ቅጣት ሲገደብ ውሳኔው ለጊዜው አለመፈጸሙ ሌላው የገደብ መሠረታዊ ጽንሰ-ሃሳብ የሚይዘው ነጥብ ነው፡፡ ፍርድቤቱ ጥፋተኝነቱን ወይም ቅጣቱን ከወሰነ በኋላ የፍርደኛው ጠባይ ከውሳኔው መፈጸም ባሻገር ሊሻሻል የሚችልበት ሁኔታ ያለ መሆኑን ያመነ እንደሆነ ለተወሰነ ጊዜ ውሳኔው እንዳይፈጸም ሊያግድ ይችላል፡፡ ውሳኔው ታገደ የሚባለውም ቅጣት ሳይፈጸም ፍርደኛው ከማህበረሰቡ ጋር ተቀላቅሎ እንዲኖር በማድረግ ሊያከብራቸው የሚገቡ ልዩ ልዩ ግዴታዎችን በማስቀመጥ ጠባዩን መፈተን የሚቻልበትን ሥርዓት መዘርጋት ሲቻል ነው፡፡ በፍርድቤቱ ውሳኔ መሠረት ፍርደኛው በተሰጠው የፈተና ጊዜ ውስጥ የተጣለበትን ግዴታ በማክበር መልካም ፍሬን ማሳየቱ የተረጋገጠ እንደሆነ በፍርዱ የተመለከተው የጥፋተኝነት ወይም የቅጣት ውሳኔ ሳይፈጸም እንዲቀር ይደረጋል፡፡

የኢትዮጵያ የወንጀል ሕግም መገደብ ወይም ማገድ የሚለውን ቃል በግልጽ ትርጉም አይስጠው እንጅ ጽንሰሃሳቡ ከላይ የተመለከቱትን መሠረታዊ ሃሳቦች አካትቷል፡፡ የመገደብ መሠረታዊ ነጥቦች፣ አይነቶች፣ ለመገደብ መሟላት ያለባቸው መሥፈርቶች፣ ፍርደኛው በሙከራ ጊዜ ሊያከብራቸው የሚገቡ ሁኔታዎችና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮች በሚቀጥሉት የጥናቱ ክፍሎች ይዳሰሳሉ፡፡

## 2. የገደብ አይነቶች

በወንጀል ሕግ ገደብ ያለውን ጽንሰ-ሃሳብ መሠረት በማድረግ ምሁራን እንደሚከተለው በሁለት ይከፍሉታል፤ የመገደብ ጽንሰ-ሃሳብ በአንዳንድ አገሮች ከክስ ጋር የሚያያዝበት አግባብ ቢኖርም[16] በዋናነት በጥፋኝነትና በቅጣት ውሳኔ ላይ ተመስርቶ ሲተገበር

---

[13] Bryan A. Garner, Blacks Law Dictionary, (7th edition, 1999), p. 1368 (ትርጉም በጸሃፊዎቹ)

[14] Ireland Law Reform Commission, Issues Paper: Suspended Sentences, 2017, p. 8. available at, https://www.lawreform.ie/_fileupload/Issues%20Papers/LRC%20IP%2012%20-%202017%20issues%20paper%20suspended%20sentences.pdf, accessed on 29 June 2019,

[15] Sarah Armstrong *et al*, International Evidence Review of Conditional (Suspended) Sentences, Final Report, 2013, REPORT No.01 /2013, p. 10 **available at** www.sccjr.ac.uk, last accessed on 13 July, 2019.

[16] Jordan Allingham *et al*, Conditional Sentences, Probation, and Discharges (No. 203), available at https://wiki.clicklaw.bc.ca/index.php?title=Special:Book&bookcmd=rendering&return_to=Conditional+Sentences%2C+Probation%2C+and+Discharges+%28No.+203%29&collection_id=f09c65013d072d1

ይስተዋላል፡፡ የመጀመሪያው የገደብ አይነት ተከሳሽ በተከሰሰበት ወንጀል ጥፋተኛ ተብሎ ፍርድ ካረፈበት በኋላ ቅጣቱን መወሰን ሳያስፈልግ ለቅጣት ውሳኔ ጊዜ የሚሰጥበት አሰራር ነው፡፡[17] በዚህ አሠራር መሠረት ወንጀለኛው በተከሰሰበት ወንጀል ጥፋተኛ እንደሆነ በማስረጃ ከመረጋገጡም በላይ የጥፋተኝነት ፍርድ ያርፍበታል፡፡[18] የጥፋተኝነቱ ውሳኔ ከተወሰነ በኋላ ቅጣቱ ሳይወሰን እንዲቆይ ይሄው ፍርድቤት ያዛል፡፡ በውሳኔውም ጥፋተኛው በፈተና ላይ እንዲቆይና በቆይታው ሊያከብራቸው የሚገቡ ሁኔታዎች አብረው ይመለከታሉ፡፡[19] በዚህ መሠረት በገደብ የተለቀቀው ጥፋተኛ እንደነገሩ ሁኔታ የተለያዩ የፍርድቤት ወጭዎችን፣ ውሳኔ ያረፈበት መቀጮና ካሳ ካለ እንዲከፍል እንዲሁም ልዩ ልዩ የማህበረሰብ አገልግሎቶችን በመስጠት ማህበረሰቡን እንዲክስ፤[20] ለተወሰነ ጊዜ በአንድ ቦታ ተወስኖ እንዲቆይ፣ ከአልኮል መጠጥ እንዲታቀብ፣ ከተወሰኑ ሰዎች ጋር ግንኙነት እንዳያደርግ፣ መልካም ባህርይ እንዲኖረውና በየጊዜው ይህንኑ ተግባር ለማስፈጸም ለተሰየመው አካል ሪፖርት እንዲያደርግ ሊወሰን ይችላል፡፡[21] ፍርዱን መሠረት በማድረግም ጥፋተኛው የወንጀለኛነት ሪከርድ ይመዘገብበታል፡፡[22] የሚቀረው ነገር ጥፋተኛው በጥፋቱ ሊወሰንበት የሚገባው ቅጣት ምን እንደሆነ አለመወሰኑ ብቻ ነው፡፡ ለቅጣት ውሳኔ ጊዜ የመስጠት ገደብ ከፍ ብሎ ከተገለጸው ከክስ ጋር ተያያዥነት ካለው ገደብና ከቅጣት ውሳኔ አፈጻጸም ገደብ የሚለይበት የራሱ ባህርያት አሉት፡፡ እነዚህም ጥፋተኛነቱ በማስረጃ ተረጋግጦ የጥፋተኝነት ውሳኔ መሠጠቱና የጥፋተኝነት ውሳኔውን መሠረት አድርጎ የወንጀል ሪከርድ መመዝገቡና የቅጣት ውሳኔ አለመተላለፉ ናቸው፡፡

ሌላው የገደብ አይነት የወንጀል ቅጣት አፈጻጸም ላይ ያነጣጥራል፡፡ በዚህ የገደብ አይነት መሠረት በተከሰሰበት ወንጀል ጥፋተኛ የተባለ ሰው ባህርይውን መሠረት ያደረጉ የቅጣት ማክበጃና ማቅለያዎች ከተመረመሩና ከተመዘኑ በኋላ ቅጣት ተወስኖበት የቅጣቱ አፈጻጸም ግን ለተሰወነ ጊዜ ታግዶ የሚቆይበት ሁኔታ ነው፡፡[23] የወንጀል ቅጣቱ ገደብ ሲታይ ግምት ውስጥ መግባት ያለባቸው ሁኔታዎች እንዳሉ የመስኩ ምሁራን ሃሳብ ያቀርባሉ፡፡ በምሁራኑ የሚቀርበው ሃሳብ የወንጀለኛው ጥፋተኝነትን መሠረት በማድረግ የእስራት ቅጣቱ ተወስኖ ተግባራዊ ከመሆኑ በፊት ወንጀለኛውን ወደ ማረሚያቤት ከመላክ ይልቅ የግል ባህርይውንና የአኗኗር ሁኔታውን በመመልከት ቅጣቱ ሳይፈጸም ከማህበረሰቡ ጋር ተቀላቅሎ ለተወሰነ ጊዜ በፈተና እንዲቆይ ማድረግ ነው፡፡[24] ይህም ሲሆን ወንጀለኛው ወደ ማረሚያቤት ሳይላክ

f&writer=rl, (last accessed 13 July , 2019). እንዲህ አይነቱ አሰራር በኮሎምቢያና በካናዳ ተግባራዊ የሚደረግ ሲሆን ተከሳሹ ክሱ እዲዘጋለት ሆኖ በድጋሜ ሌላ ወንጀል የሚፈጽም ከሆነ ገደቡ ይነሳል፡፡

[17] Sarah Armstrong *et al,* supra Note 15, p. 11.

[18] Oklahoma Statutes, Title 22. Criminal Procedure, §22-991c., Deferred sentence, available at https://law.justia.com/codes/oklahoma/2014/title-22/section-22-991c/, accessed on 13 July, 2019

[19] Arne R. Johnson, 'Recent Developments in the Law of Probation' (Jun 1962) 53(2), The Journal of Criminal Law, Criminology, and Police Science p. 195

[20] Oklahoma Statutes, supra Note 9.

[21] Jordan Allingham *et al*, supra note 16.

[22] ዝኒ ከማሁ::

[23] Sentencing Advisory Council, 'Suspended Sentence in Victoria , a preliminary Information Paper' (March 2005) p.4 available at

[24] Sara Johnson, Outcomes of Probation and Conditional Sentence Supervision: An Analysis of Newfoundland and Labrador, Nova Scotia, New Brunswick, Saskatchewan and Alberta, 2003/2004 to 2004/2005, Juristat, (Canadian Center for Justice Statistics, 2006), available, http://www.statcan2c.ca/pub/85-002-x2006007, p.3 ( last accdessed on 5 January 2019,).

በቁጥጥር ወይም ያለ ቁጥጥር ማህበረሰቡን የሚያገለግልበትና መልካም ጠባዩን የሚያሳይበት ሁኔታ ይፈጠራል፡፡ እንዲህ አይነቱ አሠራር በብዙ ሀገሮች ሕግ ተደንግጎ ይገኛል፡፡

## 3. የወንጀል ቅጣትን የመገደብ አላማ

የወንጀል ቅጣትን መገደብ በወንጀል ፍትህ አስተዳደር የተለመደ አሠራር እንደሆነና የሕግ መሠረት እንዳለው በቀደሙት የጥናቱ ክፍሎች ለማስገንዘብ ተሞክሯል፡፡ ይህ አሰራር በፍትህ ሥርዓቱ ውስጥ የተዘረጋበት ዋና አላማ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መንገድ የወንጀል ፍትህ አስተዳደር ከተመሰረተበትና ሊያሳካ ካለመው ግብ ወይም ውጤት ጋር ተያያዥነት አለው፡፡ የወንጀል ፍትህ ሥርዓቱ ዋና አላማ የአንድን አገር መንግስትና ህዝብ ሰላም፣ ጸጥታና ደህንነትን ማረጋገጥ ሲሆን[25] የፍትህ ሥርዓቱ ይህንኑ ዓላማ ለማሳካት ወንጀል እንዳይፈጸም አስቀድሞ ከመከላከል ባሻገር ወንጀል ፈጽመው የተገኙትን ሰዎች ተመጣጣኝ በሆነ ቅጣት እንዲቀጡ በማድረግ ከጥፋታቸው ታርመው መልካም ዜጋ እንዲሆኑ ይሰራል፡፡[26]

ይህን ዓላማ እውን ለማድረግ በወንጀል ሕግ ከተደነገጉ የቅጣት አይነቶች መካከል ከርእሰጉዳዩ ጋር ይበልጥ ተያያዥነት ያለው የእስራት ቅጣት ነው፡፡ ይህ የቅጣት አይነት ሲወሰን ወንጀለኛው ጥፋተኛ የተባለበት የወንጀል ክብደት፣ ግላዊ ባህርይና የተለያዩ የቅጣት ማቅለያዎች ግምት ውስጥ ገብተውና ተመዝነው ነው፡፡[27] በዚህ መሠረትም በሕጉ የተመለከተው የእስራት ቅጣት መጠን ሊቀንስ፣ በአማራጭ የቅጣት አይነት ሊተካ ወይም እንደነገሩ ሁኔታ ሊገደብ ይችላል፡፡[28] ፍርድቤቱ ከእነዚህ የቅጣት አይነቶች አንዱን ሲወስን በሕግ የተመለከቱትን የቅጣት አላማዎች ለማሳካት በማለም ነው፡፡ በተለይ የወንጀል ቅጣት ከተወሰነ በኋላ አፈጻጸሙ እንዲታገድ የሚወሰነው የእስራት ቅጣቱን ወንጀለኛው ወዲያውኑ እንዲፈጽመው ከማድረግ ይልቅ ማረሚያቤት ሳይገባ ከማህበረሰቡ ጋር ሆኖ የተጣሉበትን ሌሎች ግዴታዎች አክብሮ እንዲንቀሳቀስ በማድረግ የባህርይ ለውጥ ለማምጣትና ለሕግ ተገዥ የሆነ መልካም ዜጋ ለማድረግ የተሻለ አማራጭ እንደሆነ ሲታመንበት ነው፡፡[29]

የወንጀል ቅጣትን መገደብ ከዚህ ጋር ተያያዥነት ያላቸው በርካታ አላማዎች ያሉት ሲሆን ከዚህ ቀጥሎ ዋና ዋናዎቹን መመልከት ተገቢነት ይኖረዋል፡፡ የወንጀል ቅጣትን መገደብ ከእስራት ቅጣት መሸሽ ወይም ማምለጥ የሚመስላቸው ሰዎች ቢኖሩም[30] ቅጣትን መገደብ ከእስራት ቅጣት ዓላማ ጋር ተመሳሳይነት አለው፡፡[31] ከእስራት ቅጣት አላማዎች መካከል አንዱና ዋነኛው ወንጀለኛው ባህርይውን እንዲያሻሽል ማስቻል ነው፡፡[32] ማንኛውም ፍርድቤት

---

[25] የኢፌዴሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 1 ይመለከቷል፡፡

[26] Dean John Champion, *Sentencing A Reference Handbook* (ABC-CLIO, Inc., 2008) p. 5.

[27] Julian V. Roberts, 'Punishing, more or Less: Exploring Aggravation and Mitigation at sentencing', in Julian V. Roberts (ed), *Mitigation and Aggravation at Sentencing* (Cambridge University Press, 2011) pp. 1-2.

[28] Dean John Champion, supra note 26, pp. 35-36.

[29] Patrick Healy, 'The Punitive Nature of the Conditional Sentence, the Changing Face of Conditional Sentencing' p. 1

[30] Arie Freiberg, *Pathways to Justice: Sentencing Review, 2002, p.* 102.

[31] A. E. Bottoms, 'The Suspended Sentence in England' (January 1981) 21 (1), *the British Journal of Criminology*, p. 3

[32] Mirko Bagaric, *Punishment and Sentencing: A Rational Approach* (Cavendish Publishing Limited, London, 2001) P. 151.

*ተከሳሹ ወንጀለኛ እንደሆነ ውሳኔ ሲያስተላልፍ የወንጀለኝነት ባህርይ እንዳለውና ይሄውም መለወጥ ወይም መወገድ እንዳለበት በማመን ነው፡፡ በፍርድቤቱ የሚወሰነው ቅጣትም የወንጀለኛውን ባህርይ በማረም መልካም ዜጋ ሲያደርገው ይችላል ተብሎ ሲታመን ነው፡፡*[33] *ይህን የባህርይ ለውጥ ማምጣት የሚችሉ ቅጣቶችን ለማስፈጸም ይቻል ዘንድ በወንጀል ፍትህ ሥርዓት ውስጥ የተለያዩ የቅጣት አስፈጻሚ ተቋማት ተዋቅረው የፍትህ ሥርዓቱ አንድ አካል ሆነው እንዲሰሩ ይደረጋል፡፡ ከእነዚህም መካከል በዘመናዊ መንገድ ተደራጅተው የእስራት ቅጣትን እያስፈጸሙ ያሉ ማረሚያቤቶች ተጠቃሽና በማህበረሰቡ አስተሳሰብ እንደመቀጣጫ ተደርገው የሚወሰዱ ናቸው፡፡*[34] *በዚህም የተነሳ የእስራት ቅጣቱ ከተገደበ በተወሰነው የገደብ ጊዜ ውስጥ ባህሪውን ሲያሻሽል ለዚሁም መገለጫ ይሆን ዘንድ ሌላ ጥፋት ላይፈጽም ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶት ከእስር ሲለቀቅ በህብረተሰቡ ዘንድ በነጻ እንደተለቀቀ የሚገመትበት እይታ በብዙ አገሮች ይስተዋላል፡፡*[35] *ይሁን እንጅ የወንጀል ቅጣትን የመገደብ እሳቤ ይህንን መሠረት አያደርግም፡፡ ይልቁንም ቅጣቱ የተገደበለት ፍርደኛ የእስራት ቅጣቱን ማረሚያቤት ገብቶ አይፈጽም እንጅ ወደ ማህበረሰቡ ተቀላቅሎ እንዲኖር ሲደረግ የእስራት ቅጣት አላማውን የማሳካት ሃላፊነት አለበት፡፡*[36] *ቅጣቱ ተገድቦ ወንጀለኛው በፈተና ላይ እያለ መልካም ባህርይን ሲያሳይና ድጋሜ ወንጀል ላይፈጽም ግዴታ ይኖርበታል፡፡ በማህበረሰቡ ውስጥ ሲኖር እንዲፈጽም ከሚጠበቁበት ግዴታዎች መካከል ለተመደበለት ተቆጣጣሪ ተቋም ወይም ግለሰብ በየጊዜው ሪፖርት ማድረግ፣ በተወሰለት አካባቢ መቆየት፣ ወደ ተከለከለ ቦታ አለመሄድ፣ ከአልኮል መጠጦችና ከአደንዛዥ እጽ መቆጠብ፣ ለማህበረሰቡ አገልግሎት መስጠት፤*[37] *በአጠቃላይ ለአካባቢው ሰላም ተቆርቋሪ መሆንና ሌሎች መልካም ባህርይን ሲያስገኙ የሚችሉ ተግባራትን መፈጸም*[38] *ይገኙበታል፡፡*

*ሌላው የእስራት ቅጣት ገደብ ዓላማ እንደሆነ የሚታመነው ፍርደኛውን ሌላ ወንጀል እንዳይፈጽም የማድረግ ውጤት ነው፡፡ እንደ ማንኛውም ቅጣት ገደብ ፍርደኛው ወንጀልን ከመፈጸም የመከልከል (የማቀብ) ውጤት እንዳለው ምሁራን ያትታሉ፡፡ በሀገረ እንግሊዝ የሕግ ተንታኝ የሆነው ዴቪድ ቶማስ የእስራት ቅጣትን መገደብ ፍርደኛው ሌላ ወንጀል እንዳይፈጽም የማስጠንቀቅ አንድምታ እንዳለው ሲያስገነዝብ "የወንጀል ቅጣት ገደብ ከእስራት የተሻለ ፈጣን ውጤትን የሚያስመዘግብና ማህበራዊ ወጭንና ጫናን በመቀነስ የወንጀል ቅጣት አላማን በቀላሉ ሊያሳካ የሚችል" እንደሆነ*[39] *በአጽንኦት ይገልጻል፡፡ ተንታኙ በጽሑፉ የወንጀል ቅጣትን መገደብ ወንጀለኛው ወደፊት ሌላ ወንጀል እንዳይፈጽም የማስጠንቀቅ አላማን ያዘለ እንደሆነ ከማስገንዘቡም በላይ በአንጻሩ ከእስራት ቅጣት ባነሰ ዋጋ ይህን አላማ የማሳካት አቅም እንዳለው ያመላክታል፡፡*[40] *በሌላ አነጋገር ፍርደኛውን ጥፋተኛ*

[33] *ዝኒከማሁ፡፡*

[34] Kevin H. Wozniak, 'Perceptions of Prison and Punitive Attitudes: A Test of the Penal Escalation Hypothesis', retrieved from https://journals.sagepub.com/home, last accessed on 24 August 2019.

[35] Arie Freiberg, supra note 30,

[36] Sarah Armstrong *et al*, supra Note 15, p. 10.

[37] Conditional Sentences, Probation, and Discharges (No. 203), retrieved from https://wiki.clicklaw.bc.ca/index.php, last accessed on 24 August, 2019.

[38] Damel Ivanov Ikonomov, 'Conditional Sentencing and the Need for a Principled System of Non - Custodial Sanctions' ( A Thesis Submitted to the Faculty of Graduate Studies, In Partial Fulfillment of the Requirements For the Degree of Master of Law) P. 17.

[39] D A Thomas, 'Developments in Sentencing 1964–1973'(1974) *Criminal Law Review, pp. 685 & 688. ትርጉም በጸሃፊዎች፡:*

[40] ዝኒከማሁ።

ብሎ ወደ ማረሚያቤት በመላክ የእስራት ጊዜውን እንዲፈጽም ማድረግ በህብረተሰቡ ላይ ማህበራዊ ወጭና ጫና የሚያስከትል ሲሆን በተቃራኒው ቅጣቱን መገደብ በዝቅተኛ ወጭ የሚፈለገውን ማስጠንቀቂያ ማስተላለፍ ያስችላል።

ከፍ ብሎ እንደተገለጸው የወንጀል ቅጣትን መገደብ ወንጀለኛውን በነጻ መልቀቅ ሳይሆን የወንጀለኛውን ጥፋት በማስረጃ አረጋግጦና ቅጣት ወስኖ በማሳየት በድርጊቱ እንዲያፍርና ለወደፊቱ መሰል የወንጀል ድርጊት እንዳይጸም የማድረግ ዓላማ አለው። በዚህ አኳኋን የታለፈ ወንጀለኛ ወንጀል ፈጽሞ ጥፋተኛ የተባለና ቅጣት የተወሰነበት ቢሆንም ወደ እስርቤት ገብቶ ቅጣቱን እንዳይፈጽም በገደብ መታለፉንና ወደ መደበኛ ኑሮው መመለሱን ሲያስታውስ በድርጊቱ ይበልጥ እንደሚጸጸት ይታመናል። ይህም ወንጀለኛው ባለፈ ድርጊቱ እንዲጸጸትና እንዲያፍር በማድረግ ድጋሜ ወንጀል ካለመፈጸሙም በላይ የወንጀል ሰለባውንና ማህበረሰቡን እንዲክስና እንዲያገለግል መልካም ዜጋ ሆኖ በሰላማዊ መንገድ እንዲኖር የማድረግ ውጤት ይኖረዋል።[41]

የወንጀል ቅጣትን መገደብ ተፈጻሚ የሚሆንበት ሌላው አብይ አስፈላጊነት የአጫጭር ጊዜ እስራት ቅጣትን በማስቀረት በወንጀለኛው፣ በማህበረሰቡና በመንግስት ላይ ሊደርስ የሚችለውን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ቀውስን መቀነስ ነው።[42] እንደሚታወቀው አንድ ወንጀለኛ ጥፋተኛ ተብሎ ቀላልም ይሁን ጽኑ የእስራት ቅጣት ከተወሰነበት የቅጣቱ ጊዜ አጭርም ቢሆን[43] ወደ ማረሚያቤት እንዲገባ ይደረጋል። ይህ ሲሆን ታራሚው ለተለያዩ ማህበራዊና ኢኮኖያዊ ችግሮች ሊጋለጥ እንደሚችል ጥናቶች ያሳያሉ።[44] በማረሚያቤት ውስጥ ለሚከሰቱ አስተዳደራዊ በደሎች፣ የስነ-ምግባር ብልሽቶች እንዲሁም ለልዩልዩ የስነልቦና ችግሮች ሊዳረግ ከመቻሉም በላይ ስራን ማቋረጥና የእለት ገቢን ማጣት፣ የትዳር መፍረስ፣ የቤተሰብ መበተን፣ በማህበረሰቡ ውስጥ ያለውን ተሳትፎና ማህበራዊ ደረጃ ማጣትና ሌሎች ተያያዥ ችግሮች ያጋጥሙታል።[45] ለእነዚህ ችግሮች የተጋለጠው ወንጀለኛና ቤተሰቡ የማህበረሰቡ አካል እንደመሆናቸው መጠን የችግሩ ነጸብራቅ በማህበረሰቡ ላይ መድረሱ ሳይታለም የተፈታ ነው። ወንጀለኛው በማረሚያቤት ውስጥ እንዲቆይ መደረጉ በመንግስት ላይ የሚያደርሰው ወጭና የቦታ ጥበትም ለአጫጭር ጊዜ በሚታሰሩ ሰዎች አማካይነት መባባሱ የብዙ ማረሚያቤቶች ችግር ነው። በአጫጭር ጊዜ እስራት የተቀጡትን ሰዎች ሁሉ ወደ ማረሚያቤት እንዲገቡ ማድረጉ ከላይ የተገለጹትን ችግሮች ከማስከተሉም በተጨማሪ የእስራት ቅጣት ሊያሳካ የሚገባውን ዋና አላማ ማለትም የወንጀለኞችን ባህርይ መለወጥና መልካም ዜጋ እንዲሆኑ ማድረግ አያስችልም።

ወንጀለኞቹ ጥፋተኛ የተባሉበትን ወንጀል ለመፈጸም የገፋፋቸው ባህርይ ተለይቶ አስፈላጊውን ትምህርት በመስጠት ካለባቸው የወንጀለኝነት ባህርይ እንዲላቀቁ ለማድረግ

---

[41] Richard Fox, 'When Justice Sheds a Tear: The Place of Mercy in Sentencing' (1999) 25 (1) *Monash University Law Review* 1, 9–13 and Steven Tudor, 'Modes of Mercy' (2003) 28 *Australian Journal of Legal Philosophy* 79, 85.

[42] NSW(New South Wales) parliamentary library Research service, Probation: an overview , Briefing Paper No 21/98 ,1998 p 1 available at http://www.parliament.nsw.gov.au/gi/library/publicn.html, (last accessed 10 May ,2018).

[43] ለምሳሌ ቀላል እስራት ከ1 ቀን እስከ 3 ዓመት፣ ጽኑ እስራት ከ1 ዓመት እስከ25 አመት የሚደርስ እስራት ስለመኖሩ የኢፌዴሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 106 ጀምሮ ባሉት ድንጋጌዎች ተመልከቷል።

[44] Audrey Bazos and Jessica Hausman, correctional education as a crime control program,UCLA school of public policy and social research department of policy studies, march, 2004, p. 51.

[45] Dean John Champion, *Sentencing; a Reference Handbook (*ABC-CLIO, Inc., 2008), pp. 39-40.

በተዘረጉ የትምህርት፣ የምክርና ሌሎች መርሃ-ግብሮች እንዲያልፉ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡[46] ይሁን እንጅ የተወሰኑት የእስራት ቅጣቶች ለአጭር ጊዜ ከመሆናቸው የተነሳ ፍርደኞች በማረሚያቤት የሚኖራቸው ቆይታ ለችግር ከማጋለጥ አልፎ ያለባቸውን የወንጀለኝነት ባህርይ በመለወጥና መልካም ዜጋ በማድረግ የቅጣት አላማን ለማሳካት አያበቃም፡፡ በመሆኑም አጫጭር የእስራት ቅጣቶችን ለመፈጸም ፍርደኞችን ወደ ማረሚያቤት እንዲገቡ ከማድግ ይልቅ ቅጣቱን በመገደብ ከማህበረሰቡ ጋር ተቀላቅለው የሚጣልባቸውን ግዴታ በማክበር፣ ማህበረሰቡን በማገልገልና መልካም ዜጋ በመሆን ለሕግ ተገዥነታቸውን እንዲያሳዩ ማድረግ የተሻለ እንደሆነ በወንጀል ቅጣት ገደብ ላይ ምርምር ያደረጉ ልሂቃን ያሳያሉ፡፡[47]

አንዳንድ የዘርፉ ምሁራን ገደብ የሚያስገኛቸውን ጥቅሞች ወደጎን በመተው የወንጀል የእስራት ቅጣትን መገደብ ከወንጀል ፍትህ ሥርዓቱ መሰረዝ አለበት፤ ብለው ይሞግታሉ፡፡[48] ይሁን እንጅ ይህ ሃሳብ ከብዙ ምሁራን ተቃውሞ ገጥሞታል፡፡ የሃሳቡ ተቃዋሚ የነበረው አሾርዝ በቪክቶሪያ ግዛት እንዲቀር ተደርጎ የነበረው የወንጀል ቅጣት ገደብ ለፍርድቤቶች አማራጭ ቅጣትን እንዳሳጣ አመልክቷል፡፡ እንደዚህ ምሁር አስተሳሰብ የእስራት ቅጣት ገደብ ለፍርድቤቶች እንደ አንድ አማራጭ የቅጣት አይነት ሆኖ ማገልገሉ ፍርድቤቶች የእስራት ቅጣትን እንዳያዘወትሩ አስተዋጽኦ ይኖረዋል፡፡[49] ስለሆነም የእስራት ቅጣት ገደብ አስፈላጊነት አማራጭ ሆኖ ማገልገሉ ነው፡፡

## 4. የእስራት ቅጣት ገደብና የፈተና ጊዜው

### 4.1. የፈተና ጊዜ ምንነትና አወሳሰኑ

ስለእስራት ቅጣት ገደብ ምንነትና አስፈላጊነቱ በቀደሙት የዚህ ጥናት ክፍሎች ለማብራራት ተሞክሯል፡፡ በዚህ መሠረት የወንጀል ቅጣት ገደብ ወንጀለኛው በተከሰሰበት ወንጀል ጥፋተኛነቱ ከተወሰነ በኋላ ለቅጣት ውሳኔ ጊዜ ተሰጥቶ ወይም ቅጣት ተወስኖ ሳይፈጸም ልዩ ልዩ ግዴታዎችን እያከበረ ከማህበረሰቡ ጋር ተቀላቅሎ በፈተና እንዲቆይ የሚደረግበት አሰራር ነው፡፡ ይህ የፈተና ጊዜ ሊሰጥበት የሚችል አንድ አሰራር ይሁን እንጅ ፈተናው በሌሎችም መንገዶች ሊሰጥ ይችላል፡፡ ለምሳሌ ታራሚዎች በይቅርታና በአመክሮ ከተወሰነባቸውን የእስራት ቅጣት መጠን በከፊል በማረሚያቤት ፈጽመው ሲወጡ ቀሪ የእስራት ጊዜያቸውን በፈተና ጊዜ ውስጥ እንዲቆዩ ማድረግ በወንጀል ፍትህ አስተዳደር ውስጥ የተለመደ የማረሚያ ዘዴ ነው፡፡[50] የፈተና ጊዜ የሚሰጥበት አሠራር የተለያየ ይሁን እንጅ አስተሳሰቡና እንዲያሳካ የሚታለመው ውጤት ተመሳሳይ ነው፡፡ ይህን የበለጠ ግልጽ ለማድረግ የፈተና ጊዜ ጽንሰ-ሃሳብ ምን እንደሆነ መመልከቱ ተገቢ በመሆኑ እንደሚከተለው ለማብራራት ተሞክሯል፡፡

---

[46] Andrew Ashworth, *Sentencing and Criminal Justice (*5th ed, Cambridge University Press, 2010), P. 86.

[47] Ben S. Meeker, Probation as a Sentence, 9 Canadian J. Corrections, 1967, 281-305, p. 292,. available at https://heinonline.org/HOL/License, (last accessed on 9Jun 2019)

[48] Lorana Bartels, 'Sword or Feather? The use and utility of suspended sentences in Tasmania' (Dissertation for the Degree of Doctor of Philosophy University of Tasmania, June 2008) pp. 25-47, available at https://eprints.utas.edu.au/7735/, (last accessed 6 September 2019).

[49] ዝኒከማሁ ገጽ 16፡፡

[50] Neal Louis Mandelko, *Parole in theory and practice an evaluation of factors affecting the parole concept,* theses, Dissertations, Professional Papers, (The University of Montana, 1958) pp. 116-120. available at http://scholarworks.umt.edu/etd,( last accessed on 23 Jun 2018),

የፈተና ጊዜ በሀገረ አሜሪካ (USA) የወንጀል ፍትህ ሥርዓት ውስጥ ከ1841[51] ጀምሮ ተግባራዊ ሲደረግ የቆየ አሰራር ነው፡፡ ይሄው አሠራር የተጀመረው ጆን አውጉስተስ የተባለ አንድ አሜሪካዊ ቦስተን ፍርድቤት ተከስሶ ወደ ማረሚያቤት ሊላክ ሲል ዋስ በመሆን በእርሱ ክትትል ሥር ሆኖ የእስራት ቅጣቱን እንዲፈጽም በጠየቀው ዳኝነት መሠረት ፍርደኛው ወደ ማረሚያቤት ከሚሄድ ይልቅ በጠያቂው ሥር ሆኖ ባህርይውን እንዲያሻሽል በመወሰኑ ይሄው ተግባራዊ በተደረገበት ወቅት ነው፡፡[52] አሠራሩ በዚህ መልኩ ተጀምሮ እየሰፋና እየዳበረ በሌሎች የሰሜን አሜሪካ ግዛቶችና በአውሮፓ ይበልጥ ተግባራዊ ሆኗል፡፡[53]

ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው የፈተና ጊዜ ጽንሰ-ሃሳብ ክትትልና ቁጥጥር ያለበትና የታራሚውን መሻሻል መሰረት ያደረገ ነው፡፡ ከዚህ በታች የቀረበው ትርጓሜም ይህንኑ ሃሳብ ይበልጥ የሚያጎላ ነው፡፡

> *የፈተና ጊዜ ታራሚው የሚጠበቅበትን ግዴታ እስካሟላ ድረስ ወደእስርቤት ከሚሄድ ይልቅ በአንድ ተቆጣጣሪ የቅርብ ቁጥጥርና ክትትል ስር ሆኖ አስፈላጊውን የባህርይ መሻሻል እንዲያመጣ በፍርድቤት የሚወሰን አማራጭ የቅጣት አይነት ነው፡፡*[54]

ከዚህ መረዳት እንደሚቻለው የፈተና ጊዜ በፍርድቤት የሚወሰን የወንጀል ቅጣት ገደብ ሁኔታ በመሆኑ ታራሚው ወደ ማረሚያቤት እንዲገባ አይደረግ እንጅ በቁጥጥርና ክትትል ስር ሆኖ የቅጣት ጊዜውን እንዲፈጽም የሚገደድበት አሰራር ነው፡፡ በዚህ የፈተና ጊዜ ቁጥጥርና ክትትል ስር እንዲቆይ የሚደረግወ ፍርደኛው ታራሚ እንደመሆኑ መጠን ሊያሟላቸው የሚገቡ ቅድመ ሁኔታዎች መኖራቸው ተገልጾለት እነዚህን ማሟላትና አለማሟላቱን የሚያረጋግጥ ተቆጣጣሪ ባለሙያ ወይም ተቋም ይመደብለታል፡፡ ታራሚው ቅድመ ሁኔታዎቹን በተቆጣጣሪ ክትትል ሥር ሆኖ ሲፈጽም የባህርይ መሻሻል እያመጣ መሆኑን እንዲያሳይ ይጠበቅበታል፡፡ ሥለሆነም አንድ ታራሚ በፈተና ጊዜ ውስጥ ሲሆን እነዚህን መስፈርቶች ማሟላት እንዳለበት ከፍ ብሎ ከተሰጠው ትርጉም መገንዘብ ይቻላል፡፡

የፈተና ጊዜ በሕግ ይደንገግ እንጅ ተግባራዊ የሚሆነው በፍርድቤት ውሳኔ አማካይነት እንደሆነ ከፍ ብሎ ተመልክቷል፡፡ አንድን ወንጀለኛ በተከሰሰበት ወንጀል ጥፋተኛ ነው፤ ብሎ የወሰነ ፍርድቤት በሕጉ በተመለከተው መሠረት እንደ አስፈላጊነቱ በእስራት ወይም በሌላ የቅጣት አይነት እንዲቀጣ ሊወስን ይችላል፡፡ በእስራት ፋንታ ታራሚው በፈተና ጊዜ እንዲቆይ ማድረግ ፍርድቤቱ ባለው ፍቅድ ሥልጣን ከሚወስናቸው ቅጣቶች መካከል አንዱ ነው፡፡ ሆኖም ፍርድቤቱ እንዲህ አይነቱን ውሳኔ የሚያስተላልፈው በዘፈቀደ ሳይሆን የወንጀለኛውን የግል ባህርይ በማጥናት ከማረሚያቤት ይልቅ በፈተና እንዲቆይ ማድረጉ የተፈለገውን የቅጣት ዓላማ እንደሚያሳካ ሲታመንበት ነው፡፡ እዚህ ላይ ሊነሳ የሚገባው ነጥብ ፍርድቤቱ ያለውን ፍቅድ ሥልጣን በመጠቀም ታራሚውን በፈተና ለማቆየት ለመወሰን የታራሚውን የግል ሁኔታ አስመልክቶ መረጃዎችን የሚያገኝበት መንገድ ነው፡፡ በብዙ ሀገሮች[55] የፈተና ጊዜን የሚያስቀምጡ ሕጎች ይህንኑ ለማስፈጸም የሚያግዙ

---

[51] Sharon M. Bunzel, 'The Probation Officer and the Federal Sentencing Guidelines: Strange Philosophical Bedfellows' (Jan., 1995) 104(4) The Yale Law Journal, p. 938.

[52] ዝኒከማሁ፡፡

[53] Sharon M. Bunzel, supra Note 51, p. 936.

[54] Joan Petersilia, 'Probation in the United States' (1997) 22 Crime and Justice, p. 149 ትርጉም በጸሃፊዎች፡፡

[55] See Kenian, *Probation of Offenders Act* ( Revised Edition 2012 [1981] Published by the National Council for Law Reporting with the Authority of the Attorney-General), Section 16, Nigerian

ተቆጣጣሪ ተቋማትን አቋቁመው ከምርመራ ጀምሮ የባህርይ ለውጥ ለማምጣት የሚያስችለው የፈተና ጊዜ አፈጻጸም ድረስ ባለው ሂደት የወንጀለኛውን የግል ባህርይ እንዲከታተሉና ለሚመለከተው አካል መረጃ እንዲሰጡ ተጨማሪ ሃላፊነትን ይሰጣሉ፡፡[56] ይህ ሃላፊነት የተሰጣቸው ተቋማት ወይም ባለሙያዎቻቸው ስለወንጀለኛው የሚሰበስቡት መረጃ የፈተና ጊዜውን ለሚወስነው ፍርድቤት ግብአት ሆኖ ያገለግላል፡፡[57] ወንጀለኛው ከማረሚያቤት ይልቅ በፈተና እንዲቆይ ፍርድቤቱ ሲወስን የወንጀለኛውን የግል ባህርይ አስመልክቶ የሚቀርብለትን መረጃ በመመርመር ወንጀለኛው በፈተና ጊዜ ሲቆይ ሊፈጽማቸው የሚገቡ ግዴታዎችን በመወሰን እንደሚያሳውቀው ይጠበቃል፡፡ ታራሚው ግዴታዎችን ለመፈጸም የተስማማ እንደሆነ የፈተና ጊዜው በፍርድቤቱ ይወሰናል፡፡ ይህም በፍርድቤቱና የእስራት ቅጣት ተገድቦለት በፈተና ጊዜ እንዲቆይ በተደረገው ታራሚ መካከል የተደረገ ውል ወይም ስምምነት ሆኖ ይወሰዳል፡፡[58]

ፍርድቤቱ ታራሚው በፈተና ወቅት ሊያከብራቸው የሚገቡትን -ቅድመ ሁኔታዎች ወይም ግዴታዎች በስምምነቱ ላይ ማሳወቅ እንዳለበት ይታመናል፡፡ ታራሚው በፈተና ወቅት እንዲያከብራቸው የሚጠበቁ ሁኔታዎች በሚከተሉት ሦስት ዋና ዋና ደርዞች ሊታዩ ይችላሉ፡፡ እነዚህም፡- መደበኛ ሁኔታዎች፣ የቅጣትን ባህርይ የተላበሱና የባህርይ ለውጥን ሊያስገኙ የሚችሉ ሁኔታዎች ናቸው፡፡[59] በእያንዳንዱ ደርዝ ሥር ሊሰደሩ የሚችሉ ታራሚው በፈተናው ጊዜ ሊፈጽማቸው የሚገቡ ዝርዝር ሁኔታዎችን እንደሚከተለው በአጭሩ መመልከቱ አስፈላጊ ነው፡፡

በፈተና ጊዜ የሚቆየው ታራሚ በመደበኛነት ሊያከናውናቸው የሚገቡ ሁኔታዎች ከታራሚው የእለት ተእለት ኑሮ እንቅስቃሴ ጋር የተያያዙና በማንኛውም የፈተና ጊዜ ውሳኔ ተጠቃሚ ላይ ሊጣሉ የሚችሉ ናቸው፡፡[60] በመሰረቱ የእስራት ቅጣት ተገድቦላቸው ከማረሚያቤት ይልቅ በፈተና ላይ ሆነው ከማህበረሰቡ ጋር ተቀላቅለው እንዲቆዩ የሚደረጉ ወንጀለኞች በነጻ የተለቀቁ ሳይሆኑ በፈጸሙትና ጥፋተኛ በተባሉበት ወንጀል ምክንያት የነጻነት ገደብ ተጥሎባቸው ይህንን እንዲያከብሩ በቁጥጥርና ክትትል ስር ሆነው የተወሰነውን ጊዜ እንዲያሳልፉ የሚደረጉ እንደሆነ ቀደም ሲል ተገልጿል፡፡ በወንጀለኛው ነጻነት ላይ ከተጣሉ መደበኛ ግዴታዎች መካከል በየጊዜው ለተቆጣጣሪው ሪፖርት ማድረግ፣ የአድራሻ ለውጥን ማሳወቅ፣ ከተወሰነለት ክልል ወይም ቦታ አለመውጣት አልፈው ሲገኙም ማሳወቅ እንዲሁም የእለት ገቢ ምንጭ መፍጠር፤ የሚሉት ይገኙበታል፡፡[61]

በሁለተኛ ደረጃ ሊታዩ የሚገቡ ሁኔታዎች የቅጣትነት ባህርይ ያላቸው ግዴታዎች ናቸው፡፡ እነዚህ ሁኔታዎች የተፈጸመውን ወንጀል መሠረት በማድረግ በፈተና ላይ ባለው ታራሚ ላይ ሊጣል የሚገባውን ኃላፊነት የሚያከብዱ ናቸው፡፡ እነዚህ ግዴታዎችም ማህበረሰቡን ማገልገል፣ የወንጀል ሰለባውን መካስ፣ መቀጮ መክፈል፣ በቤት ውስጥ ተወስኖ መቀመጥና

" Administration of Criminal Justice Act, 2015", under section 453-459, Repablic of South African Probation Services Act 116 oF 1991.

[56] Peter Hungerford-Welch, *Criminal Litigation and Sentencing* (5th ed, Cavendish Publishing Limited, London, 2000) p 637.

[57] Joan Petersilia, supra Note 54.

[58] ዝኒ ከማሁ ገጽ 164፡፡

[59] ዝኒ ከማሁ፡፡

[60] ዝኒ ከማሁ፡፡

[61] ዝኒ ከማሁ፡፡

ከማንኛውም አደንዛዥ እጽ ወይም ሱስ ከሚያስይዙ ነገሮች መቆጠብና ከዚሁ ነጻ መሆናቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችል ምርመራ በየጊዜው ማድረግ ይገኙበታል፡፡[62]

በመጨረሻ ሊታዩ የሚገባቸው ሁኔታዎች ከባህርይ ለውጥ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ግዴታዎች ናቸው፡፡ ማንኛውም ታራሚ የእስራት ቅጣት ተፈርዶበት ቅጣቱን እንዲፈጽም ማረሚያቤት ሲገባ የባህርይ ለውጥ ማምጣት እንደሚጠበቅበት ሁሉ የእስራት ቅጣቱ ተገድቦለት በአንድ ተቆጣጣሪ ክትትል ሥር ሆኖ ከማህበረሰቡ ጋር የፈተና ጊዜውን እንዲያሳልፍ ሲደረግ ይህንኑ የባህርይ ለውጥ ማሳየት እንዳለበት ይታመናል፡፡ በዚህ መሠረት ፍርድቤቱ የእስራት ቅጣቱን በመገደብ የፈተና ጊዜውን ሲወስን የታራሚውን የባህርይ ለውጥ ሊያስገኙ የሚችሉ ግዴታዎችን ወይም ሁኔታዎችን አብሮ ይወስናል፡፡ በዚህ ውሳኔ መሠረት ቅጣቱ በገደብ የተወሰነለት ታራሚ ከአደንዛዥ እጽና አልኮል ጋር ተያያዥነት ባላቸው ነገሮች ለሱስ ተጋልጦ ከሆነ ከዚሁ የሚላቀቅበትን ሁኔታ እንዲፈጽም፣ የቤተሰብ ምክር አገልግሎትና የሙያ ሥልጠናዎችን እንዲከታተልና የባህርይ መሻሻል እንዲያደርግ በፍርድቤቱ ሊወሰን ይችላል፡፡[63] በአጠቃላይ ፍርድቤት ባለው ፍቅድ ሥልጣን የወንጀለኛውን ግላዊ ሁኔታ በመመርመር የእስራት ቅጣት እንዲገደብለት ሲወስን ከፍ ብሎ የተመለከቱትን ግዴታዎች ታራሚው እንዲፈጽም በግልጽ ማሳወቅና ውሳኔውን ለሚያስፈጽመው ተቆጣጣሪ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ውጤቱን እንዲያሳውቅ ትእዛዝ መስጠት ይኖርበታል፡፡

ይሁን እንጅ ፍርድ ቤቱ ትእዛዙን ሲሰጥ ታሳቢ የሚያደርጋቸው መሠረታዊ መርሆዎች እንዳሉ ማስታወሱ ተገቢ ነው፡፡ ታራሚው እንዲያከብራቸው የሚወሰኑ ግዴታዎች አላማ ተኮር፣ ምክንያታዊ፣ ሕገ-መንግስታዊና ግልጽ መሆናቸውን ውሳኔውን የሚሰጠው ፍርድቤት ማረጋገጥ ይጠበቅበታል፡፡[64] ታራሚው በእስራት ቅጣት ፋንታ በፈተና እንዲቆይ ሲወሰን የወንጀል ቅጣን አላማ ለማሳካት የሚያስችሉ ሁኔታዎች መኖራቸው መረጋገጥ አለበት፡፡ ወንጀለኛው የተወሰነበትን የእስራት ቅጣት እንዲፈጽም ማረሚያቤት ቢገባ የባህርይ ለውጥ ያመጣል ተብሎ እንደሚታመነው ሁሉ ቅጣቱ ተገድቦ በፈተና ጊዜ እንዲያልፍ ተወስኖ ከማህበረሰቡ ጋር በመቀላቀል ቅጣቱን ሲፈጽም በተመሳሳይ የባህርይ መሻሻል ማሳየት እንዳለበት ግዴታዎችን ወይም ሁኔታወችን የሚወስነው ፍርድቤት ማመን ይኖርበታል፡፡ ይህም የእስራት ቅጣቱ ተወስኖለት በፈተና ጊዜ መለቀቁ የቅጣት አላማን የሚያጠናክር እንጅ የማይቃረን መሆኑን ያስገነዝባል፡፡

የፈተና ጊዜ ውሳኔ አላማተኮር እንደሆነ ሁሉ ምክንያታዊነቱም ግምት ውስጥ መግባት አለበት፡፡ በሌላ አነጋገር በፈተና ጊዜ የተለቀቀ ታራሚ እንዲያከብራቸው የሚወሰኑ ሁኔታዎች በታራሚውም ይሁን በሌላ ምክንያታዊ ሰው ዓይን የሚጠበቁና ተቀባይነት ያላቸው መሆን አለባቸው፡፡[65] ከፍ ብሎ እንደተገለጸው የፈተና ጊዜ ተጠቃሚ የሆነው ታራሚና ውሳኔውን ያስተላለፈው ፍርድቤት ስለሁኔታዎቹ ሲስማሙ በአንድ ምክንያታዊ ሰው እይታ ግዴታዎቹ ሊፈጸሙ የሚችሉና የማይችሉ መሆናቸው መረጋገጥ ይኖርበታል፡፡ ግዴታዎቹ በምክንያታዊ ሰው እይታ የማይገመቱ ተቀባይነት የሌላቸው ከሆኑ ስምምነቱ በሕግ ፊት ዋጋ አይኖረውም፡፡ ሥለሆነም ግዴታዎችን ወይም ሁኔታዎችን በአግባቡ

[62] ዝኒ ከማሁ፡፡

[63] ዝኒ ከማሁ፡፡

[64] ዝኒ ከማሁ፡፡

[65] ዝኒ ከማሁ፡፡

በመመርመር የፈተና ጊዜ ውሳኔ ተጠቃሚ በሆነው ወንጀለኛ ተፈጻሚ ሊሆኑ የሚችሉ መሆናቸውን ማረጋገጥ ለፍርድቤቱ የተሰጠ ኃላፊነት ነው፡፡

ከዚሁ ጋር ተያይዞ ሊታይ የሚገባው ነጥብ የግዴታዎቹ ወይም የሁኔታዎቹ ሕገ-መንግስታዊነት ወይም ከወንጀለኛው ሰብዓዊ መብቶች ጋር የሚጣጣሙ የመሆናቸው ጉዳይ ነው፡፡ በወንጀል ተከስሶ ጥፋተኛ ተብሎ ቅጣት ያረፈበት ሰው እንደማንኛውም ሰው ሕገ-መንግሥታዊ ወይም ሰብዓዊ መብቶቹ እንደሚከበሩለትና ወንጀለኛ በመሆኑ ብቻ በማንኛውም አካል ሊጣሱበት እንደማይገባ ልዩ ልዩ አለምአቀፍ ድንጋጌዎች ያሰምሩበታል፡፡[66] ይህ መሠረታዊ መርህ የእሥራት ቅጣት ተገድቦ የፈተና ጊዜ ለታራሚው ሲሰጥም ተፈጻሚ ሊሆን እንደሚገባው ይታመናል፡፡[67] በመሆኑም ግዴታዎቹ ወይም ሁኔታዎቹ በፍርድቤቱ ሲወሰኑ በፈተና የተለቀቀውን ሰው መሠረታዊ መብቶች ማለትም የእምነት ነጻነት፣ የመናገር፣ ትዳር የመመስረትና ሌሎችንም መሰረታዊ መብቶች የሚጋፉ ወይም የሚቃረኑ መሆን አለመሆናቸውን ፍርድቤቱ ማረጋገጥ አለበት፡፡

በመጨረሻ የግዴታዎችን ወይም የሁኔታዎችን ህጋዊነት ለማረጋገጥ መታየት ያለበት ነጥብ ከግልጽነት ጋር የተያያዘው ነው፡፡ ግዴታዎቹ ወይም ሁኔታዎቹ በፈተና ለተለቀቀው ሰውና ለተቆጣጣሪው ግልጽ በሆነ ቋንቋ ሊነገራቸው እንደሚገባ ሁሉ የሁኔታዎቹም ይዘት ግልጽና ለመረዳት ቀላል በሆነ መንገድ ሊገለጹ ይገባል፡፡ ይህም ቅጣቱ ተገድቦለት በፈተና የተለቀቀው ወንጀለኛም ይሁን ክትትልና ድጋፍ የሚያደርገው አካል ሁኔታዎቹን ተገንዝበው ትእዛዙን በቀላሉ ለመፈጸም እንዲችሉ ያርጋል፡፡ በአጠቃላይ ግዴታዎችንና ሁኔታዎችን በመወሰን ወንጀለኛው በፈተና ጊዜ እንዲቆይ ለማድረግ የሚሰጥ ውሳኔ ሕጋዊነቱ በእነዚህ ነጥቦች መመዘን፣ ተፈጻሚነቱና ተቀባይነቱ በቅድሚያ መረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

### 4.2 የፈተና ጊዜ መሰረዝ

የፈተና ጊዜ ጽንሰ-ሃሳብንና አሰጣጥ ሁኔታን በቀደመው የጥናቱ ክፍል የተብራራ ሲሆን ቀጥሎ ይሄው የሚሰረዝበትን ሁኔታ ለመመልከት ተሞክሯል፡፡ የፈተና ጊዜ መሰረዝ ወንጀል ፈጽሞ የጥፋተኝነት ወይም የቅጣት ውሳኔ የተላለፈበት ሰው ይህንን እንዳይፈጽም ታግዶለት በፈተና ጊዜ እንዲቆይ በፍርድ የተሰጠ ውሳኔን በማንሳት የእሥራት ቅጣቱን እንዲፈጽም ወደ ማረሚያቤት እንዲገባ ማዘዝ ወይም በቅጣቱ ላይ አከራክሮ ተገቢው የቅጣት አይነት ተወስኖበት እንዲፈጽም የሚታዘዝበት ሂደት ነው፡፡[68] በሌላ አነጋገር ታግዶ የነበረው የጥፋተኝነትና የቅጣት አፈጻጸም ውሳኔ ተግባራዊ እንዲሆን የሚደረግበት የፍርድ ሂደት ነው፡፡ የፈተና ጊዜ የሚሰረዘውም ማህበረሰቡን ከወንጀል ስጋት ለመጠበቅና ወንጀለኛው በፈተና ጊዜው ባህርይዉን ባለማሻሻሉ ታግዶ የነበረውን የእስራት ቅጣት ውሳኔ እንዲፈጽም በማድረግ ከጥፋቱ እንዲታረም ለማድረግ ነው፡፡

የፈተናውን ጊዜ የሚወስነው ፍርድቤት ወንጀለኛው ጥፋተኛ መሆኑን አረጋግጦ ቅጣት ሳይወስን የጥፋተኝነት ውሳኔውን ወይም ተገቢውን የእሥራት ቅጣት ከወሰነ በኋላ አፈጻጸሙን በመገደብ የፈተና ጊዜ ሊሰጥ ሥልጣን እንዳለው ሁሉ በፈተና ጊዜ ውስጥ

[66] Heinz R. Hink, 'The Application of Constitutional Standards of Protection to Propbation' 29, *The University of Chicago Law Review,* pp. 483-497.

[67] ዝኒ ከማሁ፡፡

[68] Joel Bassett, 'Discretionary Power and Procedural Rights in the Granting and Revoking of Probation' (1969) 60(4), *The Journal of Criminal Law, Criminology, and Police Science,* p. 486,

የተካተቱ ሁኔታዎች/ግዴታዎቸ ባልተሟሉ ጊዜ የሰጠውን የፈተና ጊዜ የመሰረዝ ሥልጣን አለው፡፡ ይሁን እንጅ የፈተና ጊዜ የመስጠትና የመሰረዝ ፍቅድ ሥልጣኑ ከሁለቱ ውሳኔዎች አንጻር ሲታይ የተለያየ ነው፡፡[69] ቅጣቱን ገድቦ የፈተና ጊዜ የመስጠት ፍቅድ ሥልጣኑ ይህንኑ ከመሰረዝ አንጻር ሲታይ ሰፊ ነው፡፡ በቀደሙት የጽሑፉ ክፍሎች ለመግለጽ እንደተሞከረው ፍርድቤቱ የጥፋተኝነት ወይም የቅጣት ውሳኔ ከሰጠ በኂላ የጥፋተኛውን የግል ሁኔታ ተመልክቶ ከእስር ይልቅ የፈተና ጊዜ መስጠቱ የተሻለ የቅጣትን ዓላማ ያሳካል ብሎ ካመነ ይህንኑ የመስጠት ፍጹም የሆነ ፍቅድ ሥልጣን አለው፡፡ በዚህ መልክ የተሰጠውን የፈተና ጊዜ መሰረዝ ቢችልም ይህን የማድረግ ሥልጣኑ በአንጻሩ ውስን ነው፡፡[70]

የፈተና ጊዜውን በመሰረዝ ረገድ የፍርድቤቱ ፍቅድ ሥልጣን እንዲጠብ የተደረገባቸው ምክንያቶች ሲኖሩ ከእነዚህ መካከል አንዱና ዋነኛው የፈተና ጊዜው የሚሰረዝበት ሥነሥርዓት ኢመደበኛ በመሆኑ ፍርድቤቱ ሥልጣኑን ያለ አግባብ የመገልገሉና ስህተት የመስራት አጋጣሚው ይኖራል ተብሎ ስለሚገመት ነው፡፡[71] ፍርድቤቱ በእንዲህ አይነት አኳኂን የፈተና ጊዜውን ቢሰርዘውና ወንጀለኛውን ወደ ማረሚያቤት እንዲገባ ቢወስን በራሱ በወንጀለኛውና በማህበረሰቡ ላይ አሉታዊ ተጽእኖን ያስከትላል፡፡ የፈተና ጊዜ ዋና አላማ የወንጀለኛውን ባህርይ መለወጥና ማህበረሰቡን ከወንጀል ስጋት መጠበቅ እንደመሆኑ መጠን ፍርድቤቱ በተሳሳተ መንገድ የፈተና ጊዜውን የሚሰርዝ ከሆነ ከፍ ብሎ የተመለከተውን የፈተና ጊዜ አላማ ለማሳካት ኃላፊነት የተጣለባቸውን አካላት ማለትም ወንጀለኛውን፣ ተቆጣጣሪውንና ማህበረሰቡን በአሰራሩ ላይ ተስፋ እንዲቆርጡና እምነት እንዲያጡ ያደርጋል፡፡ ሥለሆነም ፍርድቤቱ ያለውን ፍጹም ፍቅድ ሥልጣን ተጠቅሞ በእሥራት ቅጣት ፋንታ የሰጠውን የፈተና ጊዜ ሲሰርዝ መጠንቀቅና ሥልጣኑን ውስን በሆነ መልኩ መጠቀም ይኖርበታል፡፡

ሌላው ለፍርድቤቱ ፍቅድ ሥልጣን መጥበብ ግምት ውስጥ መግባት ያለበት ነጥብ የፈተና ጊዜ የሚሰረዝበት ምክንያት ግልጽ፣ ተጨባጭና የታወቀ መሆኑ ነው፡፡ ፍርድቤቱ የፈተና ጊዜ ሲሰጥ ከወንጀለኛው የግል ሁኔታ ጋር የተያያዙ በርካታ ሁኔታዎችን[72] ግምት ውስጥ ማስገባትና መወሰን ያለበት ሲሆን የፈተና ጊዜውን ሲሰርዝ ግን ወንጀለኛው ከተጣሉበት ግዴታዎች መካከል አንዱን ወይም ከዚያ በላይ የጣሰ መሆኑን ማረጋገጥ ብቻ ይጠበቅበታል፡፡[73] ሥለዚህ የፈተና ጊዜ የመሰረዙ ጉዳይ ከመስጠቱ ይልቅ ግልጽና ተጨባጭ ምክንያት ያለው በመሆኑ የፍርድቤቱ የፈተናውን ጊዜ የመሰረዝ ሥልጣኑ እንደዚሁ ውስንና የታወቀ ነው፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ ሊነሱ የሚገቡ ጥያቄዎች ወንጀለኛው ሊያከብራቸው የሚገቡ ግዴታዎች ምንድን ናቸው? ለምን ያህል ጊዜስ እንዲያከብራቸው ይገደዳል? የሚሉት ናቸው፡፡

በመጨረሻም ለዚሁ ጉዳይ እንደምክንያት የሚነሳው የፈተና ጊዜው ዓላማ መሳካት ከዚሁ ጋር በተያያዘ መንግሥት ያለበት ግዴታ ነው፡፡ በመሰረቱ በእስራት ቅጣት ፋንታ በፍርድቤቱ የሚሰጠው የፈተና ጊዜ ዓላማ የወንጀለኛውን ባህርይ መለወጥና መልካም ዜጋ ማድረግ

---

[69] ዝኒ ከማሁ፡፡

[70] Legal Aspects of Probation Revocation (1959) 59(2) *Columbia Law Review,* p. 314,

[71] Joel Bassett, supra note 68, p. 481.

[72] ዝኒ ከማሁ ገጽ 481፡፡

[73] Legal Aspects of Probation Revocation, supra note 70, pp. 315-316.

እንደሆነ ቀደም ሲል ተገልጿል፡፡ የዚህ አላማ መሳካት አለመሳካት በፈተና ጊዜ መሰረዝ ወቅት ፍርድቤቱ ግምት ውስጥ ሊያስገባው ያስፈልጋል፡፡ ወንጀለኛው ከተጣሉበት ግዴታዎች አንዱን ሳያከብር ቢገኝ ይህንን ግዴታ አለማክበሩ ለፈተና ጊዜው መሰረዝ እንደ ብቸኛ ምክንያት አድርጎ ከመውሰድና የፈተና ጊዜውን ከመሰረዝ ይልቅ የባህርይ መሻሻል ሊያስገኙ የሚችሉ ተለዋጭ ሁኔታዎችን ሊያስቀምጥ ይችላል፡፡ ይህም የፈተና ጊዜው አላማ መሳካትን መሠረት በማድረግ ፍርድቤቱ ወንጀለኛውን በአግባቡ ማስተናገድና ተለዋጭ ግዴታዎችን በማስቀመጥ የፈተና ጊዜውን እንደችሮታ ሳይቆጥር ፍቅድ ሥልጣኑን በጠበበ መንገድ ሥራ ላይ ለማዋል በሥነ-ሥርዓት ሕግ መገደብ ይኖርበታል፡፡[74]

ብዙ የአሜሪካ ግዛቶች የፈተና ጊዜ መሰረዝን የሚመለከቱ የሥነ-ሥርዓት መብቶችን በፍርድቤቶቻቸው አማካይነት ተግባራዊ ሲያደርጉ ይስተዋላሉ፡፡[75] የፈተና ጊዜን ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ለመሰረዝ ፍርድቤቶች የተሰጣቸው ፍቅድ ሥልጣን ጠባብ ቢሆንም ይህን ሥልጣን በመለጠጥ በሚፈጸሙ ስህተቶች አማካይነት የፈተና ጊዜ ተጠቃሚ ወንጀለኞች ሊደርስባቸው የሚችለውን የመብት ጥሰት ለመከላከል የሥነ-ሥርዓት ጥበቃ ተዘርግቷል፡፡ የፈተና ጊዜ ተጠቃሚ የሆነ አንድ ወንጀለኛ የተጣለበትን ግዴታ ባለማክበሩ የፈተና ጊዜው ተሰርዞ ወደ እስርቤት እንዲመለስ ለማድረግ በቅድሚያ በጽሑፍ እንዲያውቀው መደረግ አለበት፡፡[76] ይህም የፈተና ጊዜ ተጠቃሚው ግዴታውን ማክበር አለማክበሩን በተመለከተ አስፈላውን ማስረጃ አጠናቅሮ ለሚመለከተው ፍርድቤት በማቅረብ የፈተና ጊዜ መሰረዙን ተቃውሞ እንዲከራከር ያስችለዋል፡፡ በሂደቱም የቀረበበትን ምስክር የመጠየቅ፣ መከላከያ ማስረጃ የማቅረብና የመደመጥ እንዲሁም እነዚህን ጉዳዮች ለማስረዳት በሕግ ባለሙያ የመታገዝ እድሉ ይኖረዋል፡፡[77] ሆኖም እንዲህ አይነቱ ራስን የመከላከልና የመደመጥ መብት ተፈጻሚነት በተለይም በጥፋተኝነት ውሳኔ ገደብ የመሰረዝ ሂደት ላይ ጎልቶ ይስተዋላል፡፡[78] ይህም የሆነበት ዋናው ምክንያት እንዲህ አይነቱ ገደብ ተሰርዞ በፈተና ጊዜ እንዲቆይ የተደረገው ወንጀለኛ ተመልሶ ፍርድቤት ሲቀርብ የሚጠብቀው የቅጣት ውሳኔ ክርክር ስለሚኖር መሆኑን መገንዘብ ያሻል፡፡

ከላይ በተገለጹት የክርክር ሂደት አልፎ ፍርድቤቱ የፈተና ጊዜውን ሊያሻሽለው ወይም ሊሰርዘው ይችላል፡፡ ፍርድቤቱ የፈተና ጊዜውን ሙሉ በሙሉ ከመሰረዙ በፊት የፈተና ጊዜው ተጠቃሚ ወንጀለኛ የባህርይ መሻሻል የሚያደርግበት ሌላ ሁኔታ ካለ መርምሮ ቀደም ሲል ከተጣሉበት ግዴታዎች የተለየ ሁኔታን በመወሰን ባህርይውን ሊፈትን ይችላል፡፡ ይህም ቀደም ሲል ከተወሰነው ግዴታ በተጨማሪነት እንዲፈጸም የሚደረግ በመሆኑ ወንጀለኛው በፈተና የሚቆይበትን ጊዜ የሚያራዝም ወይም የፈተናውን ሁኔታ የሚያከብድ ይሆናል፡፡ በፈተና ጊዜ እንዲቆይ የተደረገው ወንጀለኛ የተቀመጠለትን ግዴታ ባለማክበሩ የፈተና ጊዜው ሙሉ በሙሉ እንዲሰረዝ በፍርድቤቱ የተወሰነ እንደሆነ በፍርዱ ላይ የተቀመጠውን የእሥራት ቅጣት እንዲፈጽም ወደ ማረሚያቤት ይላካል፡፡[79] የፈተና ጊዜው የተሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔው ተገድቦ ቅጣቱ ሳይወሰን እንዲዘገይ ተደርጎ ከሆነ ወንጀለኛው በቀጥታ ወደ ማረሚያቤት ሊላክ አይችልም፡፡ ይልቁንም ፍርድቤቱ ቅጣቱን አስመልክቶ በማከራከር

---

[74] ዝኒ ከማሁ ገጽ 323-333፡፡

[75] Joel Bassett, supra Note 68, pp. 485-493.

[76] The Right to hearing before revocation of probation (1950) 59(8), *Yale Law journal* , pp. 1521-1529,

[77] ዝኒ ከማሁ፡፡

[78] ዝኒ ከማሁ፡፡

[79] ዝኒ ከማሁ፡፡

ተገቢ ነው፤ የሚለውን የቅጣት አይነት በመወሰን እንዲፈጸም ያደርጋል፡፡ በአጠቃላይ የፈተና ጊዜ መሰረዝ የሚያስከትለው ውጤት ወንጀለኛው የባህሪ መሻሻል እንዲያመጣ ወደ ማረሚያቤት ገብቶ የእስራት ቅጣቱን እንዲፈጽም ማድረግ፡፡

## 5. የወንጀል ቅጣትን መገደብ፡- ሕጉና አፈጻጸሙ በአማራ ክልል

### 5.1. ለቅጣት ውሳኔ ጊዜ መስጠትና ቅጣት እንዳይፈጸም ማገድ በኢትዮጵያ የወንጀል ሕግ

በቀደሙት የጥናቱ ክፍሎች እንደተመለከተው የወንጀል ቅጣትን እንዳይፈጸም ማገድ በዘመናዊ የወንጀል ሕግና ፍትህ አስተዳደር ውስጥ የዳበረ ጽንሰሃሳብና የተለመደ አሠራር እንደሆነ ለማመልከት ተሞክሯል፡፡ ለወንጀል ቅጣት ጊዜ መስጠትና ቅጣትን እንዳይፈጸም ማገድ በኢትዮጵያ የወንጀል ሕግ ተደንግጎ ከግማሽ ምዕተ-ዓመት በላይ ሲተገበር ቆይቷል፡፡ ይሁን እንጅ ጽንሰ-ሃሳቡና አሠራሩ እስካሁንም ድረስ ከብዥታ አልጸዳም፡፡[80] ሥለሆነም በሕጉና አፈጻጸሙ ላይ የሚነሱ የአረዳድ ልዩነቶችና የአፈጻጸም ችግሮች ለዚህ ጥናት መነሻ ሆነው አገልግለዋል፡፡ በርዕሰ ጉዳዩ ላይ የምርምር ድርሳናት እንደልብ ለማግኘት ለተመራማሪዎቹ ፈተና ሆኖ ያለፈ ቢሆንም በሥራ ላይ ያሉትን የሕግ ባለሙያዎችና በፍርድቤቶች የተሰጡትን ውሳኔዎች ዋቢ በማድረግ የሕጉን አተረጓጎም ክፍተትና የአፈጻጸም ችግሩን በዚህ ክፍል በአጭሩ ለመዳሰስ ተሞክሯል፡፡

ለወንጀል ቅጣት ጊዜ መስጠትና ቅጣትን እንዳይፈጸም ማገድ በኢፌዴሪ የወንጀል ሕግ በግልጽ ተደንግጓል፡፡ በዚሁ መሠረት አንድ ወንጀለኛ በተከሰሰበት ድንጋጌ ጥፋተኛ ከተባለ ወይም ቅጣት ከተወሰነበት በኋላ ውሳኔው በሕጉ በተመለከተው መሠረት ሊታገድ ይችላል፡፡[81] ውሳኔው ታግዶ እንዲቆይ ለማድረግ ግምት ውስጥ ሊገቡ የሚገባቸው ነጥቦች በሕጉ ተመልክተዋል፡፡ ማንኛውም ፍርድቤት የወሰነውን ውሳኔ ለማገድ ግምት ውስጥ ከሚያስገባቸው ነጥቦች መካከል የመጀመሪያው ወንጀለኛው ጥፋተኛ የተባለበትን ወንጀል እንዲፈጽም መነሻ የሆኑትን ምክንያቶች መመርመር ነው፡፡[82] ማንኛውም ወንጀለኛ ጥፋት እንዲፈጽም የሚገፋፉት ሥነተፈጥሯዊ፣ ሥነባህርያዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ምክንያቶች እንዳሉ ብዙ የሥነወንጀልና ማህበራዊ ሳይንስ ጠበብቶች ያስረዳሉ፡፡[83] በቅጣት ውሳኔ ወቅት የምክንያቶቹ ተለይቶ መታወቅ የወንጀለኛውን ባህርይ ለማረምና መልካም ዜጋ እንዲሆን ለማድረግ የሚያስችሉ እርምጃዎችን ለመወሰን የላቀ ፋይዳ እንዳለው ይታመናል፡፡[84] በዚህ መሠረትም የወንጀል ቅጣት ሲወሰን የወንጀለኛው የግል ባህርይና አኗኗር ሁኔታ ተጠንቶ ግምት ውስጥ መግባት እንዳለበት በኢፌዴሪ የወንጀል ሕግ ተደንግጓል፡፡[85] ይህ አይነቱ አሠራር ተግባራዊ የሚሆነው ለቅጣት ውሰኔ ጊዜ መስጠትና ቅጣት እንዳይፈጸም ታግዶ እንዲቆይ መወሰን ከወንጀለኛው ባህርይ መሻሻል ጋር ተያያዥነት ስላለው ነው፡፡ በሌላ አነጋገር በገደብ ወቅት የወንጀል መነሻ ምክንያቶች በቅድሚያ መመርመር እንዳለባቸው ሕጉ

---

[80] ዜና ሁነኛው፣ በአማራ ክልል ፍ/ቤቶች የወንጀል ቅጣትን መገደብ በሕጉና በተግባር አፈጻጸም ላይ የሚታዩ *ክፍተቶች፣ የአማራ ክልል የፍትህ አካላት ባለሙያዎች ማሰልጠኛና የሕግ ምርምር ኢንስቲትዩት የሕግ ጥናትና ምርምር መጽሔት ቁጥር 1፣* ሰኔ 2006 ዓ.ም፣ ገጽ 4፡፡

[81] የኢፊዴሪ የወንጀል ሕግ፣ በግርጌ ማስታዎሻ ቁጥር 2 እንደተገለጸው፣ አንቀጽ 190፡፡

[82] ዝኒ ከማሁ፡፡

[83] Stephen E. Brown *et al, Criminology: Explaining Crime and Its context ( 7th ed,* Anderson Publishing, 2010) pp. 135-357.

[84] Patrick R. Anderson and Donald J.Newman, *Introduction to criminal justice* (5Th ed, McGraw Hill, New York and others,1993) p. 287.

[85] የኢፊዴሪ የወንጀል ሕግ፣ በግርጌ ማስታዎሻ ቁጥር 2 እንደተገለጸው፣ አንቀጽ 188፡፡

የደነገገው ቅጣቱ ለታገደለት ወንጀለኛ ባህርይ መሻሻል የሚያግዙ የጥንቃቄ እርምጃዎች ሲወሰዱ ግምት ውስጥ መግባት ስላለባቸው ነው፡፡

ሌላው የወንጀል ቅጣት ውሳኔ ሲገደብ ፍርድቤቱ ማረጋገጥ ያለበት ነገር የቅጣቱ መገደብ የወንጀለኛውን ጠባይ ለማረምና ለማሻሻል እንዲሁም ወደመደበኛ ማህበራዊ ኑሮው ለመመለስ የሚኖረው ፋይዳ ነው፡፡[86] ወንጀለኛው በተከሰሰበት ወንጀል ጥፋተኛ ተብሎ ቅጣት የሚወሰንበት ዋናው ምክንያትም ባህርይውን እንዲያሻሽልና መልካም ዜጋ ሆኖ መደበኛ ኑሮውን እንዲመራ ለማስቻል በመሆኑ የገደቡ አላማ ከዚሁ ማፈንገጥ የለበትም፡፡ ይልቁንም ፍርድቤቱ የወንጀለኛው መቀጣትና የቅጣቱ መገደብ ተመሳሳይ አላማና ግብ ያላቸው መሆኑን ተገንዝቦ ለቅጣት ውሳኔ ጊዜ መስጠትም ይሁን ቅጣት እንዳይፈጸም ማገድ የወንጀለኛውን የባህርይ ለውጥ ማስገኘት የሚችል ስለመሆኑ በቂ ማረጋገጫ ሊኖረው እንደሚገባ ከዚሁ ድንጋጌ[87] መገንዘብ ይቻላል፡፡ ውሳኔው የታለመውን መልካም ፍሬ ወይም ውጤት ለማስገኘት የወንጀለኛውን መልካም ፈቃድ ይጠይቃል፤ ሲፈጸምም ውጤት ማስገኘት ካልቻለ ሊሰረዝ ይችላል፡፡[88] ሕጉ ይህንን መርህ መሠረት በማድረግ ለቅጣት ውሳኔ ጊዜ መስጠትና ቅጣት ቅጣት እንዳይፈጸም ማገድ እንደሚቻል በአንቀጽ 191 እና 192 ላይ በግልጽ ደንግጎ ይገኛል፡፡ አንቀጽ 191 ለቅጣት ውሳኔ ጊዜ ስለሚሰጥበት አግባብ ሲያወሳ አንቀጽ 192 ደግሞ የተወሰነው ቅጣት እንዳይፈጸም የሚታገድበትን ሁኔታ ያሳያል፡፡ የሁለቱ የገደብ አይነቶች ይዘት ምን እንደሚመስል ቀጥሎ በአጭሩ ለማሳየት ተሞክሯል፡፡

### 5.1.1 ለቅጣት ውሳኔ ጊዜ መስጠት

ከሁለቱ የገደብ አይነቶች አንዱ የሆነው ለቅጣት ውሳኔ ጊዜ መስጠት እንደ ሌሎቹ አገሮች ሁሉ በኢትዮጵያ ሕግ ውስጥም ተደንግጎ እንደሚገኝ ከኢፌዴሪ የወንጀል ሕግ መረዳት ይቻላል፡፡ በዚሁ ሕግ አንቀጽ 191 ላይ እንደተመለከተው አንድን የወንጀል ጉዳይ በዳኝነት የሚመለከት ፍርድቤት ጉዳዩን መርምሮ ወንጀለኛው ጥፋተኛ ሆኖ ሲያገኘው የጥፋተኝነት ውሳኔ መስጠትና[89] ተመጣጣኝ የቅጣት ውሳኔ ማስተላለፍ የሕጉና የፍርድቤቶች አሠራር መርህ ነው፡፡ ሆኖም የተከሳሹን ባህርይ ወይም የግል ሁኔታ አጢኖ ከቅጣት ውሳኔ መለስ ሊያስተምረው የሚችል እርምጃ ያለ እንደሆነ ሲያምን ለቅጣት ውሳኔ ጊዜ ሊሰጥ ይችላል፡፡ በሌላ አነጋገር ተከሳሹን ጥፋተኛ ብሎ ቅጣት ከማስተላለፍ ይልቅ ማስጠንቀቂያ ሰጥቶ የቅጣት ውሳኔውን ቢያዘገየው ተከሳሹ የቅጣት ውሳኔ ሳያርፍበት የባህርይ መሻሻል ሊያመጣ እንደሚችል ካመነ በፈተና ጊዜ እንዲቆይ ሊያዝዝ ይችላል፡፡[90] ከዚህ መገንዘብ የሚቻለው ፍርድቤቱ የቀረበለትን ክስና ማስረጃ መርምሮ ተከሳሹ በተከሰሰበት ወንጀል ጥፋተኛ እንደሆነ የሚያረጋግጥ ማስረጃ ሲያገኝ የጥፋተኝነት ውሳኔ አሳልፎ በጥፋተኛው ላይ ቅጣት ለመወሰን ጊዜ ሊሰጥ እንደሚችል ነው፡፡ ይሁን እንጅ ከዚህ ጋር በተያያዘ በሕግ ባለሙያዎች መካከል የሀሳብ ልዩነቶች ይስተዋላሉ፡፡ ብርሃነ ገብረእግዚአብሄር የተባለ አንድ የሕግ ባለሙያ ሦሥት የገደብ አይነቶች እንዳሉ ሲገልጽ ለጥፋተኝነት ውሳኔም ጊዜ ሊሰጥ እንደሚችል

---

[86] ዝኒ ከማሁ፣አንቀጽ 190፡፡

[87] ዝኒ ከማሁ፡፡

[88] ዝኒ ከማሁ፡፡

[89] የኢትዮጵያ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነስርአት፣ አዋጅ ቁጥር 185/1954፣ ነጋሪት ጋዜጣ (1954)፣ አንቀጽ 149/1፡፡

[90] የኢፌዴሪ የወንጀል ሕግ፣ በግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 2 እንደተገለጸው፣ አንቀጽ 191፡፡

ይገልጻል፡፡[91] ጸሐፊው በኢፌዴሪ የወንጀል ሕግ ቁጥር 191 ሁለተኛው አንቀጽ ሥር የተመለከተውን ድንጋጌ መነሻ በማድረግ በሕጉ ከተመለከቱ ገደቦች ውስጥ አንዱ ከጥፋተኝነት ውሳኔ በፊት ሊደረግ የሚችል የገደብ አይነት እንደሆነ ያብራራል፡፡ ይሁን እንጅ የሕጉ መንፈስ በጥንቃቄ ሲመረመር ከጥፋተኝነት ውሳኔ በፊት ሊታገድ የሚችል ነገር እንደሌለ መገንዘብ ይቻላል፡፡ በመሠረቱ የጥፋተኝነቱ ውሳኔ ካልተወሰነ በቀር ሊታገድ የሚችለው ነገር ምን ሊሆን ይችላል? ሥለዚህ ከድንጋጌው መገንዘብ የሚቻለው ፍርድቤቱ ጉዳዩን መርምሮ የጥፋተኝነት ውሳኔ ከሰጠ በኋላ ወደቅጣት ውሳኔ መሄድ ሳያስፈልገው በዚሁ የባህርይ መሻሻል ሊያሳይ እንደሚችል ካመነ በፈተና ጊዜ እንዲቆይ ሊወስን ይችላል፡፡ በፈተና ጊዜው እንዲቆይ የተደረገ ወንጀኛ የውሳኔው መልካም ፍሬ የሆነውን የባህርይ መሻሻልና ለውሳኔው ተገዥ መሆንን በተግባር ካሳየ የጥፋተኝነት ውሳኔው ሙሉ በሙሉ ተሰርዞ ፍርዱ እንዳልነበረ ይቆጠራል፡፡[92]

እንዲህ አይነቱን የገደብ ውሳኔ መሥጠት የፍርድቤቱ ፍቅድ ሥልጣን ይሁን እንጅ ሥልጣኑን ተጠቅሞ ለቅጣት ውሳኔው ጊዜ ሲሰጥ የወንጀለኛውን ባህርይ መመዘን እንዳለበት ይሄው ድንጋጌ ያሳያል፡፡ ፍርድቤቱ ለቅጣት ውሳኔው ጊዜ ለመስጠት ማየት ከሚጠበቅበት ነጥቦች መካከል አንዱ የወንጀለኛው ጠባይ አደገኛ አለመሆኑን ነው፡፡[93] በተጨማሪም ወንጀለኛው ከዚህ ቀደም ወንጀል ፈጽሞ የተቀጣ አለመሆኑን ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡ የወንጀለኛውን ጠባይ እነዚህን ሁኔታዎች መሠረት በማድረግ ከመረመረና መሟላታቸውን ካረጋገጠ በኋላ ወንጀለኛው ጥፋተኛ የተባለበትን የወንጀል አይነትና ለወንጀሉ በሕጉ የተመለከተውን ቅጣት ማየት ይጠበቅበታል፡፡[94] በዚህም መሠረት ጥፋተኝነቱ ተወስኖ ለቅጣት ውሳኔ ጊዜ የሚሰጠው ወንጀለኛው ጥፋተኛ የተባለበት የወንጀል አይነት በመቀጮ[95]፣ በግዴታ ሥራ[96] ወይም ከሶስት ዓመት በማይበልጥ ቀላል እሥራት የሚያስቀጣ ሆኖ የተገኘ እንደሆነ ነው፡፡[97] ለቅጣት ውሳኔ ጊዜ ለመስጠት ወንጀለኛው ጥፋተኛ የተባለበት የወንጀል አይነት በድንጋጌው ከተዘረዘሩት የቅጣት አይነቶች አንጻር ሲታይ ቀላል የሚባል መሆን እንዳለበት መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ ምክንያቱም መቀጮ፣ የግዴታ ሥራ ወይም ከሶስት አመት በታች በሚሆን ቀላል የእሥራት ቅጣት እንዲቀጡ የሚደረጉ ወንጀለኞች ቀላል የወንጀል ድርጊት የፈጸሙ፣ አደገኛ ባህርይ የሌላቸውና ጠባያቸውን በቀላሉ ማረም የሚችሉ እንደሆኑ የወንጀል ሕግ መርህ ስለሚያስቀምጥ ነው፡፡[98] የወንጀሎቹ ይዘት ቀላል መሆኑ ብቻ ሳይሆን የጥፋተኛው ባህርይ አደገኛ ያልሆነና በቀላሉ ሊታረም የሚችል የመሆኑ ጉዳይም የማይዘነጋ ነው፡፡ ይህንን መሠረት በማድረግ ወንጀለኛው ተከስሶ ጥፋተኛ የተባለበት ድንጋጌ መቀጮ፣ የግዴታ ሥራ ወይም ከሶስት ዓመት የማይበልጥ ቀላል እሥራት ሆኖ ሲገኝ ለቅጣት ውሳኔ ጊዜ መስጠትን ለመወሰን

[91] Berhane Gebregziher, 'Conditional Suspension of Penalty under the Ethiopian Criminal Code: What Is Missing?'(June 2017) 5(1), *Mekelle University Law Journal,* p. 67.

"….The first possibility is to enter no conviction when a criminal is placed on probation and does not break the conditions of his probation. In this case, the conviction of guilty/not guilty may be suspended…."

[92] የኢፌዴሪ የወንጀል ሕግ፣ በግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 2 እንደተገለጸው፣ አንቀጽ 191፡፡

[93] ዝኒ ከማሁ፡፡

[94] ዝኒ ከማሁ፡፡

[95] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 90፡፡

[96] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 104 እና 105፡፡

[97] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 191፡፡

[98] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 90፣ 103፣ 106 እና 179 ይመለከቷል፡፡

ተግባራዊ እንዴት ይሆናል? የሚለው የፍርድ ቤቱን የሕግ ትርጉም የሚሻ ነው፡፡ የድንጋጌው አቀራረፅ ሲታይ ከሦሥቱ የቅጣት ዓይነቶች በአንዱ በሚያስቀጣ ድንጋጌ ተከስሶ ጥፋተኛ የተባለ እንደሆነ ለቅጣት ውሳኔ ጊዜ ሊሰጥ እንደሚችል የሚያመላክት ይመስላል፡፡ በሌላ በኩል ተከሳሹ ጥፋተኛ የተባለበት ድንጋጌ ከአማራጭ ይልቅ ተደራራቢ ቅጣትን ማለትም መቀጮና የእሥራት ቅጣትን በአንድ ላይ የሚያዝዝ ቢሆንም ቅጣቱን ከመገደብ የሚከለክል ሁኔታ በሕጉ ስላልተመለከተ መሰል የጥፋተኝነት ውሳኔ ሊታገድ እንደሚችል ይታመናል፡፡

እንዲህ አይነቱ ገደብ በሕጉ በግልጽ ይመልከት እንጅ በአማራ ክልል ፍርድቤቶች በብዛት ሲተገበር አይስተዋልም፡፡[99] ለዚህ ጥናት ዓላማ ቃለ-መጠይቅ ከተደረገላቸው ዳኞች መካከልም ብዙዎቹ እንዲህ አይነቱ አሰራር እንደሌለ ሲገልጹ በተለይ ቃለ-መጠይቁን ከሰጡን ባለሙያዎች አንዱ በረጅም ጊዜ የዳኝነት ቆይታው በአንድ ጉዳይ ላይ ብቻ ለቅጣት ውሳኔ ጊዜ መስጠቱን የሚያስታውስ መሆኑን አብራርቷል፡፡[100] ከዚህም መገንዘብ የሚቻለው ለቅጣት ውሳኔ ጊዜ መስጠትን አስመልክቶ በኢፌዴሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 191 ላይ በግልጽ ይደንገግ እንጅ ሕጉ በስራ ላይ አለመዋሉን ነው፡፡ የማይተገበርበት ምክንያትም የተለየያ ሲሆን በዋናነት የሚጠቀሱት የዳኞች የግንዛቤ ክፍተት[101]፣ ለአፈጻጸም የሚኖረው አስቸጋሪነትና[102] ቅጣቱ ቢወሰን የሚኖረው ፋይዳ ናቸው፡፡[103] ለቅጣት ውሳኔ ጊዜ መስጠት ለአፈጻጸም አስቸጋሪ እንደሆነ የገለጹ ዳኞች ጉዳዩን ሲያብራሩ መዝገቡ ያለቀ ወይም የተዘጋ እንደማይመስላቸው፣ ያላለቀውን መዝገብ መልሶ ለማከራከር ሊያጋጥማቸው የሚችለውን ችግር በማሰብ ቅጣትን ወስኖ መገደብ የተሻለ እንደሆነ ያምናሉ፡፡[104] ለጥናቱ መረጃ ሰጪ ሆነው በተሳተፉ ብዙዎቹ ዳኞች እንደ ምክንያት የቀረበው ሌላው ነጥብ ለቅጣት ውሳኔ ጊዜ መስጠት የማይተገበረው ለጥፋተኛውም ይሁን ለማህበረሰቡ የሚያስተላልፈው ማስጠንቀቂያ ወይም ትምህርት ፋይዳው የጎላ ባለመሆኑ ነው፡፡ ለቅጣት ውሳኔ ጊዜ ተሰጥቶ ጥፋተኛው ሲለቀቅ የፈጸመው ወንጀል የሚያስቀጣውን የቅጣት መጠን ባለማወቁ በውሳኔው ፈርቶ እራሱን እንደጥፋተኛ የመቁጠሩና ወደፊት መሰል የወንጀል ድርጊቶችን ከመፈጸም የመቆጠቡ እድል ጠባብ ከመሆኑም በላይ በማህበረሰቡ ዘንድ በነጻ እንደተለቀቀ ይገመታል፡፡[105] ለቅጣት ውሳኔ ጊዜ መስጠት በሌሎች አገሮችም እንደዚሁ የማይዘወተር ሲሆን ይሄው የማይሆንበት ምክንያትም ከፍ ብሎ ከተሰጠው ምክንያት ጋር ተመሳሳይነት አለው፡፡ ለምሳሌ፣ በሀገረ አሜሪካ ለቅጣት ውሳኔ ጊዜ ከመስጠት ይልቅ የቅጣት አፈጻጸምን ማገድ ይዘወተራል፡፡ ለዚህም እንደ ምክንያት የሚነሳው ለቅጣት ውሳኔው የተሰጠው ጊዜ ገደብ በልዩ ልዩ ምክንያት ቢሻር ወይም ቢሰረዝ ቅጣትን ለመወሰን በሚደረገው ክርክር ወቅት በዳኞች ላይ ሊያስከትል የሚችለውን አሉታዊ ተጽእኖ ወይም አድሎ ለመከላከልና

[99] ዜና ሁነኛው፣ በግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 80፣ ገጽ 33፡፡

[100] አቶ ተካበ አይነኩሉ፣ ዳኛ በምስራቅ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍርድቤት ፣ የወንጀል ቅጣት ገደብን አስመልክቶ የተደረገ ቃለመጠይቅ፣ 6/6/2011 ዓ.ም፡፡

[101] ሂወት ታደሰ፣ ዳኛ ጉባላፍቶ ወረዳ ፍርድቤት ፣ በወንጀል ቅጣት ገደብ ላይ በጽሁፍ የተሰጠ ቃለመጠይቅ፣ 21/8/2011 ዓ.ም፡፡

[102] ደረበ አበበ፣ ዳኛ ጉባላፍቶ ወረዳ ፍርድቤት ፣ በወንጀል ቅጣት ገደብ ላይ በጽሁፍ የተሰጠ -ቃለመጠይቅ፣ 21/8/2011 ዓ.ም፡፡ ፡፡

[103] አቶ ብርሃኑ አሰፋ፣ ዳኛ ደቡብ ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት፣ በወንጀል ቅጣት ገደብ ላይ በጽሁፍ የተሰጠ ቃለመጠይቅ፣ 29/8/2011 ዓ.ም፡፡

[104] አቶ ጋሻው ሞላ፣ ዳኛ ማእከላዊ ጎንደር ዞን ከፍተኛ ፍርድቤት ፣ በወንጀል ቅጣት ገደብ ላይ የተሰጠ ቃለመጠይቅ፣ 6/6/2011 ዓ.ም፡፡

[105] አቶ ይሄነው ጌታቸው፣ ዳኛ ሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድቤት ፣ በወንጀል ቅጣት ገደብ ላይ የተሰጠ ቃለመጠይቅ፣ 6/6/2011 ዓ.ም፡፡

ጥፋተኛውም ይሁን ማህበረሰቡ በወንጀለኛው ላይ የተጣለው ቅጣት ከታወቀ በኋላ አፈጻጸሙ ቢገደብ የሚያስገኘውን ማስጠንቀቂያና አስተምህሮት ለማስገንዘብ ነው፡፡[106]

ለቅጣት ውሳኔ ጊዜ መስጠት በአማራ ክልል ፍርድቤቶች በተለያዩ ምክንያቶች የተለመደ ባይሆንም አልፎ አልፎ ሊፈጸም እንደሚችል ለዚህ ጥናት ዓላማ ከተደረገው ቃለ-መጠይቅና የቡድን ውይይት መገንዘብ ይቻላል፡፡ ለቅጣት ውሳኔ ጊዜ ሲሰጥ የመስፈርቶቹን አማራጭ ወይም ተደማሪ መሆን ከፍ ብሎ የሕጉን አተረጓጎም በተመለከተ በተሰጠው ማብራሪያ ላይ እንደተመለከተው አንዳንዶቹ ዳኞች አማራጭ ናቸው፤ ሲሉ ሌሎቹ ደግሞ ተደማሪ እንደሆኑ ይገልጻሉ፡፡ ወንጀለኛው ጥፋተኛ የተባለበት ድንጋጌ መቀጮና የእሥራት ቅጣትን የሚደነግግ ከሆነ የወንጀሉን ከባድነት ስለሚያሳይ ለቅጣት ውሳኔው ጊዜ መስጠት የለበትም የሚል ክርክር በአንድ በኩል[107] በሌላ በኩል ደግሞ ድንጋጌው መቀጮ፣ የግዴታ ሥራ ወይም የእሥራት ቅጣት ሲደነግግ ከሶስቱ አንዱን ቅጣት ማስተላለፍ እንደሚቻል ለማሳየት እንጅ ወንጀሉን ለማክበድ እንዳልሆነ በማብራራት ለቅጣት ውሳኔ ጊዜ መስጠት ክልከላ ምክንያት እንደማይሆን ይነሳል፡፡[108] ይህም ሕጉን አስመልክቶ ዳኞች ያላቸው ግንዛቤ የተለያየ እንደሆነ የሚያሳይ ነው፡፡ የዚህ ጥናት አቅራቢዎችም ለቅጣት ውሳኔ ጊዜ ለመስጠት እንደመስፈርት የተመለከቱት ሶስቱ የቅጣት አይነቶች ማለትም መቀጮ፣ የግዴታ ሥራና ከሶስት አመት የማይበልጥ ቀላል እስራት ጥፋተኛው ከሶስቱ በአንዱ የሚቀጣ ከሆነ ለቅጣት ውሳኔ ጊዜ ሊሰጥ እንደሚችል ለማሳየት እንጅ መቀጮና የእስራት ቅጣት ተደማሪ ሆነው ቢመጡ የቅጣት ውሳኔ ሊሰጥ እንደማይችል ለማሳየት እንዳልሆነ ያምናሉ፡፡

### 5.1.2 የወንጀል ቅጣት እንዳይፈጸም ማገድ

የወንጀል ቅጣት እንዳይፈጸም ማገድ የሚነሳው ወንጀለኛው ሊፈፅመው የሚገባው ቅጣት ከተወሰነ በኋላ ነው፡፡ ጉዳዩን በዳኝነት የሚያየው ፍርድቤት የቀረበለትን ክስ ተቀብሎ በማከራከር ተከሳሹን ጥፋተኛ ሆኖ ካገኘው የጥፋተኝነት ውሳኔ ያሳርፋል፤ ይህ ውሳኔ ጊዜ የሚሰጠው ከሆነ ግን ለቅጣት ውሳኔ ጊዜ ሊሰጥ እንደሚችል ከፍ ብሎ ተገልጿል፡፡ ፍርድቤቱ ይህን ማድረጉ መልካም ፍሬ እንደማያስገኝ ካመነ በቅጣቱ ላይ ግራ ቀኙን አከራክሮ ቅጣት እንደሚወስን በኢትዮጵያ ወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ተደንግጓል፡፡[109] ከሁለቱም ተከራካሪ ወገኖች ማለትም ከዐቃቤ ሕግና ከተከሳሹ እንደ ቅደምተከተላቸው የቅጣት ማክበጃና ማቅለያ ምክንያቶችን ተቀብሎ በመመዘን የቅጣቱን መጠን ከወሰነ በኋላ የተወሰነው ቅጣት ወዲያውኑ ይፈጸም ወይስ ይቆይ የሚለውን ጭብጥ መርምሮ ሲወስን ቅጣት **እንዳይፈጸም ማገድ** የሚለው ነጥብ ይነሳል፡፡ ለዚህ ጥያቄ ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል ድንጋጌ በኢፌዴሪ የወንጀል ሕግ ከአንቀጽ 192 ጀምሮ ባሉ ድንጋጌዎች ተመልክቷል፡፡ በዚህ መሠረት ማንኛውም ፍርድቤት የወንጀል ቅጣትን ከወሰነ በኋላ አፈጻጸሙን ለማገድ ሥልጣን ተሰጥቶታል፡፡ ይሁን እንጅ እንዲህ አይነት ውሳኔዎችን ለመገደብ ከዚህ በታች የተመለከቱት መስፈርቶች መሟላታቸውን ማረጋገጥ ይጠበቅበታል፡፡

---

[106] በግርጌ ማስታዎሻ ቁጥር 73 የተመለከተውን ጽሁፍ በድጋሜ ይመለከቷል፡፡

[107] በአማራ ክልል ከሚገኙ የወረዳና ከፍተኛ ፍርድቤት ዳኞች ጋር የተደረገ ቡድንተኮር ውይይት፣ 8/6/2011 ዓ.ም፡፡

[108] በአማራ ክልል ከሚገኙ የወረዳና ከፍተኛ ፍርድቤት ዳኞች ጋር የተደረገ ቡድንተኮር ውይይት፣ 8/6/2011 ዓ.ም፡፡
አቶ ብርሃኑ አሰፋ፣ ዳኛ ደቡብ ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት፣ በወንጀል ቅጣት ገደብ ላይ በጽሁፍ የተሰጠ ቃለመጠይቅ፣ 29/8/2011 ዓ.ም፡፡

[109] የኢትዮጵያ ወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነስርአት፣ በግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 89 እንደተገለጸው፣ አንቀጽ 149፡፡

ፍርድቤቱ የወሰነውን ቅጣት እንዳይፈጸም ከማገዱ በፊት ቅጣት ስለሚገደብለት ሰው ባህርይ እውቅና ሊኖረው ይገባል። ፍርድቤቱ የቅጣት ውሳኔው እንዲታገድለት የጠየቀውን ሰው የቀድሞ ታሪኩን፣ ጠባዩን፣ አኗኗሩንና የሥራ ሁኔታውን ቅጣቱን ከማገዱ አስቀድሞ ማወቅ እንደሚያስፈልግ ባመነ ጊዜ ማስረጃ እንዲቀርብለት ማዘዝ ይኖርበታል።[110] የቀረበለትን ማስረጃ በአግባቡ በመመርመርና በማጣራት የቅጣት ውሳኔው እንዲታገድለት የጠየቀውን ሰው አመል ምንነት ማረጋገጥና የቅጣት ገደብ ውሳኔውን መስጠት አለበት።[111] በዚህ መሠረት የአማራ ክልል ፍርድቤቶች የቅጣት አፈጻጸምን ለመገደብ የወንጀለኛውን አመል ለመገምገም የሚያስችሉ ሁኔታዎችን ግምት ውስጥ ያስገባሉ። ለዚህ ጥናት ዓላማ የተሰበሰቡ የፍርድ መዛግበት እንደሚያሳዩት ፍርደኛው ከግል ተበዳይ ጋር እርቅ መፈጸሙና ካሳ መክፈሉ፣ በፈጸመው የወንጀል ድርጊት መጸጸቱና ጥፋተኝነቱን በፍርድቤት ማመኑ እንዲሁም ሌሎች የወንጀለኛውን አመለሸጋነት የሚያሳዩ ሁኔታዎችን የቅጣት ውሳኔን ለመገደብ እንደ አሳማኝ ምክንያት ሆነው ይወሰዳሉ።[112] በተጨማሪም የፍርድ መዛግብቱ ዳኞች የቅጣት ውሳኔን ሲገድቡ የፍርደኛውን የግል ሁኔታ ማለትም የጤና ሁኔታውንና የቤተሰብ አስተዳዳሪነቱን ግምት ውስጥ እንደሚያስገቡ ያሳያሉ።[113] ከተለያዩ የአማራ ክልል ፍርድቤቶች ከተውጣጡ ዳኞች ጋር የተደረገው ቡድን ተኮር ውይይትም ይሁን ቃለ-መጠይቅ ይህንኑ እውነታ የሚያሳይ ነው።[114]

የቅጣት እንዳፈጸም መገደብ ለፍርድቤት የተሰጠ ፍቅድ ሥልጣን ይሁን እንጂ ይህንን ሥልጣን በመጠቀም የቅጣት አፈጻጸሙን ገድቦ ወንጀለኛው በፈተና ጊዜ እንዲቆይ ለማድረግ ሌላ መታየት ያለበት ጉዳይ የወንጀሉ ይዘትና ወንጀለኛው ከዚህ ቀደም ወንጀል ፈጽሞ የተፈረደበት መሆን ያለመሆኑ ነው። በመርህ ደረጃ ጥፋተኛው ከዚህ ቀደም ወንጀል ፈጽሞ የተቀጣ ስለመሆኑ ሪከርድ ቢኖርበትም የገደብ ተጠቃሚ ከመሆን የሚከለክለው ነገር አለመኖሩን ከኢፌዴሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 192 መገንዘብ ይቻላል። ይሁን እንጅ ይህ መርህ ከዚሁ ሕግ አንቀጽ 194 አንጻር ሲታይ የቅጣት አፈጻጸም ገደብን ያለምንም ክልከላ ለፍርድቤቱ የተተዎ አይደለም። ይልቁንም ማንኛውም ፍርድቤት የወሰነው ቅጣት እንዳይፈጸም ሲያግድ በዚሁ ድንጋጌ የተመለከቱትን መሪ ሃሳቦች መመርመርና የተወሰነው ቅጣት አፈጻጸሙ ሊታገድ የሚችል መሆን አለመሆኑን ማረጋገጥ ይጠበቅበታል። በድንጋጌው እንደተመለከተው ወንጀለኛው ለመጀመሪያ ጊዜ ጥፋተኛ የተባለ ሰው እንደሆነ የወንጀሉ ይዘት የትኛውንም አይነት የእስራት ቅጣት[115] የሚያስከትል ቢሆንም የቅጣት

---

[110] ዝኒከማሁ፣ አንቀጽ 195።

[111] የኢፌዴሪ ጠቅላይ ፍርድቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የወንጀል ቅጣት እንዳይፈጸም ማገድን አስመልክቶ የሰጣቸውን አስገዳጅ ውሳኔዎች ከመዝገብ ቁጥር 94404 (ቅጽ 16)፣ 85596 (ቅጽ 15)፣ 46382 (ቅጽ 9) እና 34280 (ቅጽ 7) ላይ ይመለከቷል።

[112] በ ዐ/ሕግና በተከሳሽ እብራሂም ካሳ መካከል በተከፈተ የወንጀል ክርክር መዝገብ ላይ በደሴ ከተማ ወረዳ ፍርድቤት የተሰጠ ውሳኔ፣ የወንጀል መዝገብ ቁጥር 16231፣ ሰኔ 3 ቀን 2011 ዓ.ም።

በዐ/ሕግ እና በተከሳሽ አህመድ ካሳየ መካከል በተከፈተ የወንጀል ክርክክር መዝገብ ላይ በደሴ ከተማ ወረዳ ፍርድቤት የተሰጠ ውሳኔ፣ የወንጀል መዝገብ ቁጥር 16310፣ ግንቦት 23 ቀን 2011 ዓ.ም።

[113] ዐ/ሕግ እና በተከሳሾች አቶ አሰፋ ሰኢድናአረጉ አህመድ መካከል በተከፈተ የወንጀል ክርክር መዝገብ ላይ በአልብኮ ወረዳ ፍርድቤት የተሰጠ ውሳኔ፣ የወንጀል መዝገብ ቁጥር 0201680፣ ግንቦት 19 ቀን 2011 ዓ.ም።

[114] በአማራ ክልል ከሚገኙ የወረዳና ከፍተኛ ፍርድቤት ዳኞች ጋር የተደረገ ቡድንተኮር ውይይት፣ 8/6/2011 ዓ.ም።

ተካበ አይነ ኩሉ፣ ይሄነው፣ጋሻው ሞላ፣ ሂዎት ታደሰ፣ ብርሃኑ አሰፋና ሌሎችም የምስራቅ ጎጃም፣ ሰሜን ሸዋ፣ ሰሜን ጎንደር፣ ሰሜን ወሎና ደቡብ ወሎ ከፍተኛና ወረዳ ፍርድቤት ዳኞች ጋር የተደረገ ቃለመጠይቅ፣ በየካቲና በሚያዝያ ወር 2011 ዓ.ም።

[115] በኢፌዴሪ የወንጀል ሕግ አነቀጽ 106-108 የተመለከቱት የእስራት ቅጣት አይነቶች የተመለከቱ ቀላልና ጽኑ የእስራት አይነቶችን ይመለከቷል።

አፈጻጸም ሊገደብ ይችላል፡፡ ሆኖም ለመጀመሪያ ጊዜ ጥፋተኛ የተባለው ሰው በፍርድቤቱ የተወሰነበት ቅጣት ከአምስት አመት የሚበልጥ ጽኑ እሥራት ከሆነ ቅጣቱ ሊገደብ አይችልም፡፡[116] ይህም ፍርድቤቶች የቅጣት አፈጻጸምን ለመገደብ በሕግ የተሰጣቸውን ፍቅድ ሥልጣን በመጠቀም እጅግ ከባድ የሆኑ ወንጀሎችን ፈጽመው ጥፋተኛ የተባሉ ሰዎችን በገደብ በመልቀቅ በህዝብ ደህንነትና ጥቅም ላይ ስጋት እንዳይፈጠር ለማድረግ ነው፡፡[117] ይህ አነጋገር ወንጀለኛው ከዚህ ቀደም በሌላ ወንጀል ጥፋተኛ ተብሎ ቅጣት የተወሰነበት ቢሆን ፍርድቤቱ እንደገና ጥፋተኛ ተብሎ የተወሰነበትን ቅጣት ሊያግድለት አይችልም፤ ማለት ግን አይደለም፡፡[118] ከዚህ መገንዘብ የሚቻለው ወንጀለኛው ጽኑ እስራት፣ ከ3 ዓመት የሚበልጥ ቀላል እስራት ከዚህ ቀደም ያልተወሰነበት ከሆነና አሁን በተከሰሰበት ወንጀልም ከእነዚህም ቅጣቶች በአንዱ የማይቀጣ የሆነ እንደሆነ የእስራት ቅጣቱ ሊገደብለት ይችላል፡፡[119] ይህም ፍርድቤቱ ጥፋተኛ ብሎ ቅጣት የወሰነበትን ፍርደኛ ቅጣቱ እንዲታገድለት ሲወስን ከዚህ ቀደም ይሄው ወንጀለኛ በፍርድቤት በጽኑ እስራት ያልተቀጣ መሆኑን ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡ ከዚህ ቀደም ተከስሶ ጥፋተኛ በተባለበት ወንጀል በሕጉ የተመለከተውን ከአንድ ዓመት ጀምሮ የሚያስቀጣ ጽኑ እሥራት[120] ተፈርዶበት መሆኑ ከተረጋገጠና አሁን ጥፋተኛ ተብሎ የተወሰነበት ቅጣት ጽኑ እስራት ወይም ከሦሥት ዓመት የሚበልጥ ቀላል እሥራት ከሆነ ሊገደብለት አይችልም፡፡ በተቃራኒው የአሁኑ ቅጣት እስከሦስት ዓመት የሚደርስ ቀላል እሥራት ከሆነ ግን ፍርድቤቱ የወሰነውን ቅጣት እንዳይፈጸም በማገድ በፈተና ጊዜ እንዲቆይ ሊወስን ይችላል፡፡ ከዚህ ቀደም በወንጀል ጥፋተኛ ተብሎ ከሦሥት ዓመት በሚበልጥ ቀላል እሥራት እንዲቀጣ የተወሰነበት ወንጀለኛም አሁን እንደገና በተከሰሰበት አዲስ ወንጀል ጥፋተኛ ተብሎ በዚሁ እስራት ወይም በጽኑ እስራት እንዲቀጣ የተወሰነ እንደሆነ ቅጣቱ እንደማይገደብ ከዚሁ ድንጋጌ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ነገርግን ጥፋተኛው ከዚህ ቀደም የተቀጣው እስከሦስት ዓመት በሚደርስ ቀላል እስራት ከሆነና አሁንም በተከሰሰበት ወንጀል ተመሳሳይ ቅጣት ተወስኖበት ከሆነ ቅጣቱ ሊገደብለት እንደሚችል ከዚሁ ድንጋጌ ተቃራኒ ንባብ መረዳት ይቻላል፡፡

የወንጀለኝነት ሪከርድ ያለበት ጥፋተኛ ከላይ በተመለከቱት መስፈርቶች መሰረት የቅጣት አፈጻጸም ገደብ ሊጠቀም የሚችል ይሁን እንጅ የወንጀለኛው ባህርይ አደገኛና ደጋጋሚ ወንጀለኛ መሆኑ ከተረጋገጠ የወንጀል ቅጣት ገደብ ይከለከላል፡፡[121] ፍርድቤቱ ቅጣቱን ሲወስን የወንጀለኛውን ባህርይ አስመልክቶ በቀረቡለት ማስረጃዎች አደገኛ ባህርይ ያለውና ደጋጋሚ ወንጀለኛ መሆኑን ያረጋገጠ እንደሆነ የቅጣት አፈጻጸሙን መገደብ እንደማይችል ድንጋጌው በግልጽ ያመለክታል፡፡ እዚህ ላይ በጥንቃቄ ሊመረመር የሚገባው ነጥብ ጥፋተኛ ተብሎ ቅጣት የተወሰነበትና አፈጻጸሙ እንዲታገድለት ጥያቄ ያቀረበው ጥፋተኛ የደጋጋሚነትና የወንጀለኝነት ሪከርድ ጉዳይ ነው፡፡ በኢፌዴሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 67 እና 188 መሠረት አንድ ሰው ደጋጋሚ ወንጀለኛ የሚባለው የተወሰነበትን የወንጀል ቅጣት ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ፈጽሞ፣ በይቅርታ ወይም በአመክሮ ከእስር ከተለቀቀበት ጊዜ ጀምሮ ባሉት አምስት አመታት ውስጥ ከስድስት ወር በሚበልጥ ቀላል እሥራት የሚያስቀጣ ወንጀል ሆን ብሎ ፈጽሞ ጥፋኛ ተብሎ የተቀጣ እንደሆነ እንደደጋጋሚ ወንጀለኛ

---

[116] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 194 (1)(ለ)፡፡

[117] የኢፌዴሪ የወንጀል ሕግ፣ ሐተታ ዘምክንያት፣ ገጽ 106፡፡

[118] የኢፌዴሪ የወንጀል ሕግ፣ በግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 2 እንደተገለጸው፣ አንቀጽ 192ን ይመለከቷል፡፡

[119] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 194(1)(ሀ)፡፡

[120] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 108 ይመለከቷል፡፡

[121] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 194(1)፡፡

ስለሚቆጠር የወንጀል ቅጣት አፈጻጸሙ ሊገደብለት አይችልም፡፡ በመሆኑም ማንኛውም ፍርድቤት ደጋጋሚነትና የወንጀል ሪከርድ ጽንሰ-ሃሳብን ከሕጉ አንጻር በአግባቡ በመመርመር የገደብ ውሳኔን መስጠት ይኖርበታል፡፡ በአጠቃላይ የወንጀል ቅጣት አፈጻጸም መገደብን በተመለከተ ሕጉ በግልጽ ያስቀምጥ እንጂ በአማራ ክልል ፍርድቤቶች ሲተገበር ሕጉን በመረዳት ረገድም ይሁን በአተገባበሩ ላይ ችግሮች ይስተዋላሉ፡፡ በተለይ የወንጀል ቅጣት አፈጻጸሙን ገደብ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል የፈተና ጊዜና ተቆጣጣሪ እንደሚያሻ ሕጉ ቢያስቀምጥም ይሄው ምን ያህል ተግባራዊ እየሆነ ነው የሚለውን ከዚህ ቀጥሎ ባለው የጽሑፉ ክፍል ሲብራራ ችግሩ ይበልጥ ይጎላል፡፡

## 6 የፈተና ጊዜ፣ ቁጥጥሩና የፈተናው ፍሬ አለማስገኘት የሚያስከትለው ውጤት

በቀደሙት የጥናቱ ክፍሎች እንደተመለከተው ማንኛውም ፍርድቤት ወንጀለኛውን ጥፋተኛ ካለ ወይም ቅጣትን ከወሰነ በኋላ ለቅጣት ውሳኔ ጊዜ ሊሰጥ ወይም ቅጣቱ እንዳይፈጸም ሊገድብ ይችላል፡፡ ሆኖም ፍርድቤቱ ይህን ሊያደርግ የሚችልበት ፍቅድ ሥልጣን ቢኖረውም ምክንያቱን መግለጽ ይጠበቅበታል፡፡[122] ይህም ፍርድቤቱ ያለውን ፍቅድ ሥልጣን በዘፈቀደ ወይም ያለገደብ እንዳይጠቀምበት ለማድረግ ታስቦ የተቀመጠ ይመስላል፡፡ ፍርድቤቱ እንዲህ አይነቱን ውሳኔ ሲሰጥ በሕጉ የተመለከቱ መስፈርቶች መሟላት አለመሟላታቸውን መመዘን አለበት፡፡ በዚህም መሠረት ፍርድቤቱ የፈተና ጊዜን ሲወስን ወንጀለኛው በተሰጠው የፈተና ጊዜ ተጠቅሞ በመልካም ጠባይ አመራር እንደሚመራ፣ የተሰጠውን ግዴታ እንደሚቀበል፣ የወንጀሉ ሰለባ በሆኑ ሰዎች ላይ ያደረሰውን ጉዳት እንደሚክስ እንዲሁም የፍርድቤቱን ወጭ እንደሚከፍል ሲያምንበት መሆን ይኖርበታል፡፡[123] ለዚህ ማረጋገጫ ይሆን ዘንድም ፍርድቤቱ በገደብ የሚለቀቀውን ሰው ዋስትና እንዲያቀርብ ያስገድደዋል፡፡ የዋስትና አይነቱም የሰው ዋስ ወይም በንብረትና በገንዘብ መያዣ ሊሆን እንደሚችል በሕጉ በግልጽ ተመልክቷል፡፡ ይሁን እንጂ በሕጉ ላይ የተመለከቱት ሁኔታዎች ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ ሲደረጉ አይስተዋሉም፡፡ በተለይም በገደብ የሚለቀቀው ሰው ለመፈጸም የተቀበለውን ግዴታ በስምምነቱ መሠረት ተግባራዊ እንደሚያደርግ ዋስትና ማቅረብ እንዳለበት በሕጉ የተመለከተ ቢሆንም በአማራ ክልል ፍርድቤቶች ይሄው ተግባራዊ ሲሆን አይስተዋልም፡፡[124]

የመስፈርቶችን መሟላት አረጋግጦ ቅጣቱ እንዳይፈጸም መታገድ አለበት፤ ብሎ ያመነ ፍርድቤት ፍርደኛው የሚቆይበትን የፈተና ጊዜ ይወስናል፡፡ በሕጉ የተመለከተው የፈተና ጊዜ ከሁለት ዓመት እስከ አምስት ዓመት ካለው ጊዜ አንዱን መወሰን ለፍርድቤት የተሰጠ ሥልጣን በመሆኑ የፈተና ጊዜው ሁለት፣ ሦስት፣ አራት ዓመት አልያም በዚሁ የጊዜ ገደብ ውስጥ ሌላ ጊዜ ለመወሰን የወንጀለኛውን ባህርይ መረዳት ያሻል፡፡ ለዚህም ወንጀለኛው የፈጸመው ወንጀል ክብደት፣ የወንጀሉ ተደጋግሞ መፈፀም ሊያደርስ የሚችለው ጉዳትና በጥፋተኛው ላይ ሊጣልበት የሚችለው እምነት በአግባቡ መመዘን ይኖርበታል፡፡[125] እነዚህን ሁኔታዎች ለመረዳት የወንጀለኛውን የቀድሞ ባህርይ፣ አኗኗር ሁኔታ እድሜና ሌሎችንም መመርመርና መመዘን ተገቢ ነው፡፡[126] የወንጀለኛው ሁኔታ ተመዝኖ የፈተና ጊዜው ቢሰጥ

[122] ዝኒ ከማሁ፣ አንጽ 196፡፡

[123] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 197፡፡

[124] በግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 113 እና 114 የተመለከቱ የፍርድ መዛግብት፡፡

[125] የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የወንጀል ሕግ፣ አንቀጽ 196(2)፡፡

[126] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 88፡፡

መልካም ፍሬ ለማምጣት የሚያስችል መሆኑ ከታመነበት ከሁለት ዓመት የማያንስ ከአምስት ዓመት የማይበልጥ የፈተና ጊዜ ይሰጣል፡፡ ሕጉ ከሁለት እስከ አምስት ዓመት ሊደርስ የሚችል የፈተና ጊዜ ሊሰጥ እንደሚችል ይደንግግ እንጅ በአማራ ክልል ፍርድቤቶች ሁለት ዓመት የፈተና ጊዜ ብቻ እንደሚሰጥ አሰራሩ ያሳያል፡፡[127] ይህንኑ ይበልጥ ለመገንዘብ በአማራ ክልል ፍርድቤቶች ከተሰጡ ውሳኔዎች የተወሰኑትን በመምረጥ ለማየት ተሞክሯል፡፡ ለዚህ አላማ በተመረጡ ሁሉም ውሳኔዎች ላይ የተሰጠው የፈተና ጊዜ በሕጉ የተቀመጠው ዝቅተኛው የፈተና ጊዜ ማለትም ሁለት ዓመት ሆኖ ይታያል፡፡ ለአብነትም የደሴ ከተማ ወረዳ ፍርድቤት በቀላል አካል ጉዳት ማድረስና በሥርቆት ወንጀሎች ተከሰው ጥፋተኛ በተባሉና አራት ወርና በአንድ አመት ከሁለት ወር ቀላል እስራት ተወስኖባቸው በገደብ እንዲለቀቁ ለተደረጉ ሁለት ወንጀለኞች በተመሳሳይ የሁለት ዓመት የፈተና ጊዜ በመስጠት የእሥራት ቅጣቱን እንዲገደብ አድርጓል፡፡[128] ይህም የተለየያ መጠን ያላቸው ቅጣቶች ተመሳሳይ የሆነ የፈተና ጊዜ በፍርድቤቶች የሚሰጥ መሆኑን ያሳያል፡፡ በመሠረቱ በፍርድቤት የሚወሰን የወንጀል ቅጣት መጠን ከፍና ዝቅ ማለት የወንጀለኛውን ባህርይና የወንጀሉን ክብደት ታሳቢ ያደረገ መሆኑን መገንዘቡ ቀላል ነው፡፡ ይሁን እንጅ በአማራ ክልል ፍርድቤቶች የፈተና ጊዜ ሲወሰን በሕጉ የተመለከተውን ከሁለት እስከ አምስት ዓመት የሚደርስ የፈተና ጊዜ እንደ ወንጀሉ ክብደትና በወንጀለኛው ላይ ሊጣል የሚችለው እምነት መሰረት ተደርጎ ሊወሰን ሲገባው በዚህ ጥናት ለአብነት ተወስደው በተዳሰሱ ሁሉም ውሳኔዎች ላይ በሕጉ የተመለከተው ዝቅተኛ የፈተና ጊዜ ሁለት ዓመት ያለ ልዩነት ሲወሰን ተስተውሏል፡፡ እንዲህ አይነቱ ውሳኔ ከሕጉ ጋር የተጣረሰ ነው፤ ባይባልም እንኳ የወንጀለኛውን ባህርይና የተፈጸመውን ወንጀል ክብደት መሠረት በማድረግ የተወሰነ ባለመሆኑ በሕጉ የታለመውን መልካም ፍሬ ሙሉ በሙሉ ያስገኛል ለማለት አያስደፍርም፡፡ በመሆኑም በሕጉ የተመለከተው ከሁለት እስከ አምስት አመት የሚደርስ የፈተና ጊዜ በፍርድቤቱ ሲወሰን ለሁሉም ወንጀል አይነቶችና ወንጀለኞች ተመሳሳይ ሁለት ዓመት መሆን ሕጉ ሊያሳካ የሚፈልገውን ዓላማ በማስገኘት ረገድ የራሱ የሆነ አሉታዊ ውጤት ስለሚኖረው ፍርድቤቶች የፈተና ጊዜ ሲወሰኑ የወንጀሉን ክበደትና የወንጀለኛውን ባህርይ ግምት ውስጥ በማስገባት የተለያየ የፈተና ጊዜ መወሰን እንዳለበት መገንዘብ ይኖርባቸዋል፡፡

የፈተና ጊዜ ሲወሰን በገደብ የተለቀቀው ሰው ሊፈጽማቸው የሚገቡ ደንቦች አብረው ሊወሰኑ ይገባል፡፡ ምክንያቱም ወንጀለኛው በፈተና ጊዜ እንዲቆይ ሲደረግ የሚጠበቀው ውጤት የባህርይ መሻሻል ስለሆነ ነው፡፡ ይህንኑ ውጤት ለማስገኘት በፈተና ጊዜ እንዲቆይ የተደረገው ሰው በዚህ ጊዜ ውስጥ ሊከተላቸው የሚገቡ የጠባይ አመራር ደንቦች ሊገለጹለት ወይም እንዲያውቃቸው ሊደረግ ይገባል፡፡ ከእነዚህ የጠባይ አመራር ደንቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ የሙያ ሥልጠና መውሰድ፣ በአንድ በተወሰነ ሥፍራ መቀመጥ፣ የመስራት ወይም የመኖር ግዴታ፣ ከአንዳንድ ሰዎች ጋር ያለመገናኘት፣ አልኮል ከመጠጣት መከልከል፣ ከሚያገኘው ገቢ ለሞግዚቱ ወይም ለአሳዳሪው መስጠትና ሌሎች መሰል ግዴታዎች ናቸው፡፡[129] በፈተና ጊዜ ወቅት ወንጀለኛው በእነዚህ ደንቦች ህይዎቱን መምራት እንዳለበት በሕጉ መደንገጉ ወንጀለኛው በፈተናው ጊዜ ባህርይውን የማሻሻል ግዴታ ስላለበት በእነዚህ

[127] በአማራ ክልል ከሚገኙ የወረዳና ከፍተኛ ፍርድቤቶች ለጥናቱ ከተመረጡ ዳኞች ጋር የተደረገ ቡድንተኮር ወይይት፣ 8/6/2011 ዓ.ም፡፡ ተካበ አይነ ኩሉ፣ ይሄነው፣ጋሻው ሞላ፣ ሂዎት ታደሰ፣ ብርሃኑ አሰፋና ሌሎችም የምስራቅ ጎጃም፣ ሰሜን ሸዋ፣ ሰሜን ጎንደር፣ ሰሜን ወሎና ደቡብ ወሎ ከፍተኛና ወረዳ ፍርድቤት ዳኞች ጋር የተደረገ ቃለመጠይቅ፣ በየካቲትና እ በሚያዝያ ወር 2011 ዓ.ም፡፡

[128] በ ዐ/ሕግና በተከሳሽ እብራሂም ካሳ፣ የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 112 እና የደሴ ከተማ ወረዳ ፍርድቤት በመዝገብ ቁጥር 02-16159 ላይ የተሰጠ ውሳኔ፡፡

[129] የኢፌዴሪ የወንጀል ሕግ፣ አንቀጽ 198 (1)፡፡

ደንቦች መሠረት እንዲንቀሳቀስ ለማድረግ ነው፡፡ እነዚህን ደንቦች ማክበር አለማክበሩን ለማረጋገጥ አንድ ተቆጣጣሪ መመደቡ እንደተጠበቀ ሆኖ[130] የወንጀለኛውን አቅምና ፍላጎት፣ የነገሩ ሁኔታና ጥፋቱ ያደረሰውን ጉዳት ግምት ውስጥ ማስገባት ተገቢ እንደሆነ በሕጉ በግልጽ ተመልክቷል፡፡[131] የነገሩ ሁኔታና በወንጀል ድርጊቱ የደረሰው ጉዳት ተመዝኖ በፈተና ጊዜ እንዲቆይ የተወሰነበት ሰው ሊከተላቸው የሚገቡ የጠባይ አመራር ደንቦችን ወይም ሊፈጽማቸው የሚገቡ ግዴታዎችን ለይቶ በፍርዱ ላይ በመግለጽ ቁጥጥር እንዲደረግባቸው ለማዘዝ ወንጀለኛው ግዴታዎችን ለመፈጸም ያለው አቅምና ፍላጎት በፍርድቤቱ ግንዛቤ ውስጥ መግባት አለበት፡፡ የቁጥጥሩ ወይም የግዴታዎቹ በፍርዱ መለየት ዋና ዓላማ የወንጀለኛውን ባህርይ ማሻሻል እስከሆነ ድረስ እነዚህ ግዴታዎች ሲወሰኑ ከገደቡ ውሳኔና ሕግ ጋር የማይጣረሱ መሆናቸውን ማረጋገጥም የፍርድቤቱ ኃላፊነት ነው፡፡ ግዴታዎቹን ለመፈጸም ወንጀለኛው አቅምና ፍላጎት ያለው እና ግዴታዎቹም የወንጀለኛውን ባህርይ ለማሻሻል ፋይዳ ያላቸው ከሆነ በፍርድቤቱ የቅጣት ውሳኔውን ገድቦ ወንጀለኛው በፈተና ጊዜ እንዲቆይ ማድረጉ በሕጉ የተመለከተውን የወንጀል ቅጣት ዓላማን በማሳካቱ ረገድ ትልቅ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡ በዚህ ጥናት የተመለከትናቸው የፍርድቤት ውሳኔዎች ወንጀለኛው ቅጣቱ በሁለት አመት የተገደበለት መሆኑን ከመግለጽ በቀር በዚህ ጊዜ ውስጥ ሊከተላቸው የሚገቡትን የጠባይ አመራር ደንቦችና እነዚህኑ ለመፈጸም ያለውን አቅምና ፍላጎት ፍርድቤቶች ግምት ውስጥ እንደማያስገቡ ያሳያሉ፡፡[132] ይህንኑ ጉዳይ በተመለከተ ከተለያዩ ፍርድቤቶች ከተውጣጡ ዳኞች ጋር የተደረገው ቃለመጠይቅና ቡድን ተኮር ውይይት እውነታውን ያረጋግጣል፡፡[133] ከተሰበሰበው መረጃ መገንዘብ እንደሚቻለው ከላይ የተመለከቱትን ሕጉ የሚያዝዛቸው የጠባይ አመራር ደንቦች ተግባራዊ የማይሆኑበት ዋናው ምክንያት ሕጉ በሚያዝዘው መሠረት የጠባይ አመራር ደንቦቹን አፈጻጸም የሚቆጣጠር ተቋም ወይም ባለሙያ በፍትህ ሥርዓቱ ውስጥ ያለመኖሩ ነው፡፡[134] በዚህ ምክንያት ብዙዎቹ ዳኞች የጠባይ አመራር ደንቦችን በፍርዳቸው ላይ ገልጸው በወንጀለኛው እንዲፈጸሙ አያዝዙ እንጅ አልፎ አልፎ የአመራር ደንቦችን በግልጽ ሳያመለክቱ በደምሳሳው የገደብ ውሳኔ አፈጻጸምን ፖሊስ ወይም ቀበሌ እንዲከታተለው ትእዛዝ ሲሰጡ ይስተዋላል፡፡[135] ሆኖም የተሰጡት ትእዛዞች ይፈጸሙ አይፈጸሙ ፍርድቤቱ የሚከታተልበት አሰራር ስለሌለ የተሰጠው ትእዛዝ ያስገኘውን ውጤት በተመለከተ ፍርድቤቱ መረጃ የለውም፡፡[136]

---

[130] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 199፡፡

[131] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 198 (2)፡፡

[132] በ ዐ/ሕግና በተከሳሽ እብራሂም ካሳ፣ የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 112 እና የደሴ ከተማ ወረዳ ፍርድቤት በመዝገብ ቁጥር 02-16159 ላይ የተሰጠ ውሳኔ፡፡
በዐ/ሕግና በተከሳሽ አህመድ ካሳየ መካከል በተከፈተ የወንጀል ክርክክር መዝገብ ላይ በደሴ ከተማ ወረዳ ፍርድቤት የተሰጠ ውሳኔ፣ የወንጀል መዝገብ ቁጥር 16310፣ ግንቦት 23 ቀን 2011 ዓ.ም፡፡
ዐ/ሕግ እና በተከሳሾች አቶ አሰፋ ሰኢድና አረጉ አህመድ መካከል በተከፈተ የወንጀል ክርክር መዝገብ ላይ በአልብኮ ወረዳ ፍርድቤት የተሰጠ ውሳኔ፣ የወንጀል መዝገብ ቁጥር 0201680፣ ግንቦት 19 ቀን 2011 ዓ.ም፡፡

[133] የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 127 ይመልከቱ፡፡

[134] አቶ ጌትየ አድማሴ፣ በአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድቤት የሰበር ሰሚ አጣሪ ችሎት ዳኛ፣ የወንጀል ቅጣት ውሳኔ ሲገደብ በፍርዱ ሊገለጽ ስለሚገባው የጠባይ አመራር ደንብን አስመልክቶ የተደረገ ቃለመጠይቅ፣ መስከረም ሁለት ቀን 2012 ዓ.ም፡፡ አቶ ሃሚድ ሙላት፣ ዳኛ በጎንደር ዙሪያ ወረዳ ፍርድቤት ፣ ስለ ጠባይ አመራር ደንቦች የተደረገ ቃለመጠይቅ፣ ጳጉሜ 5 ቀን 2011 ዓ.ም፡፡

[135] አቶ ተካበ አይነኩሉ፣ ዳኛ ምስራቅ ጎጃም ከፍተኛ ፍርድቤት ፣ በአመራር ደንብ ዙሪያ የተደረገ ቃለመጠይቅ፣ 26/6/2011 ዓ.ም፡፡

[136] ዝኒ ከማሁ፡፡

በኢፌዴሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 200 እና 194 (2(ሐ)) ላይ በግልጽ እንደተመለከተው የተሰጠው የፈተና ጊዜ መልካም ፍሬ እንደማያስገኝ ፍርድቤቱ የተረዳ እንደሆነ ገደቡን እስከመሻር ሊደርስ የሚችል ውሳኔ ሊሰጥ እንደሚችል በግልጽ ተመልክቷል፡፡ ከእነዚህ ድንጋጌዎች መገንዘብ እንደሚቻለው ፍርድቤቱ የጥፋተኝነትን ወይም የቅጣት ውሳኔውን ገድቦ የፈተና ጊዜ የሚሰጠው ይሄው መልካም ፍሬ ያስገኛል፤ ብሎ ለማመን የሚያስችለው ማስረጃ ሲገኝ ነው፡፡ ሆኖም የተጠበቀው መልካም ፍሬ ላለመገኘቱ ማሳያ የሆነው የመልካም ጠባይ አመራር ደንብ ሲጣስ ወይም ወንጀለኛው ሌላ ወንጀል ፈጽሞ ሲገኝ ፍርድቤቱ ቀደም ሲል በሰጠው የገደብ ውሳኔን ባላከበረው ሰው ላይ ማስጠንቀቂያ ሊሰጥ ወይም የፈተና ጊዜውን ሊያራዝም አልያም ይህንኑ በመሻር ቅጣት ወስኖ ወይም ቀደም ሲል የተወሰነውን የእሥራት ቅጣት እንዲፈጽም ሊያዝዝ ይችላል፡፡[137]

በፈተና ጊዜ እንዲቆይ የተወሰነለት ሰው በፍርድቤቱ እንዲያከብራቸው የተወሰኑትን የጠባይ አመራር ደንቦች ለምሳሌ አልኮል አለመጠጣት፣ በተወሰነ ሥፍራ ታግዶ መቆየት፣ የሙያ ሥልጠና መውሰድ፣ ሰርቶ ከሚያገኘው ገቢ የተወሰነውን ለአሳዳጊው ወይም ለሞግዚቱ መስጠት፣ የታዘዘለትን ህክምና መከታተልና ሌሎች መሰል በፍርዱ የተገለጹ ትእዛዞችን ጥሶ የተገኘ እንደሆነ ወይም በቸልተኝነት ወንጀል ፈጽሞ የተገኘ እንደሆነ በዚሁ ወንጀል መከሰሱ እንደተጠበቀ ሆኖ ፍርድቤቱ ጉዳዩን መርምሮ ማስጠንቀቂያ ሊሰጠው ይችላል፡፡ ይህም የሚሆነው ከላይ ከተመለከቱት የአመራር ደንቦች አንዱን ወይም ከዚያ በላይ የሆነውን ጥሶ የተገኘው ወይም በቸልተኝነት ሌላ ወንጀል ፈጽሞ የተገኘ ወንጀለኛ በማስጠንቂያ ቢታለፍ ሊማር ይችላል ተብሎ በፍርድቤቱ ሲታመን ነው፡፡ ከማስጠንቀቂያው ይልቅ ሌላ አዲስ የጠባይ አመራር ደንብ ወይም የፈተና ጊዜውን ማራዘም የወንጀለኛውን ጠባይ ለማሻሻል አስፈላጊ መሆኑን ፍርድቤቱ ያመነበት እንደሆነ የፈተና ጊዜውን ከመሻሩ በፊት ይህን የመሰለ እርምጃ እንዲወሰድ ሊታዘዝ ይችላል፡፡[138]

ወንጀለኛው በእነዚሁ እርምጃዎች ሳይማር በመጥፎ ጠባዩ የቀጠለ ወይም ሆነ ብሎ ሌላ ወንጀል የፈፀመ እንደሆነ የተወሰነለት የቅጣት አይነት ገደብ ተሽሮ የእሥራት ቅጣቱን እንዲፈጽም ከመደረጉም በላይ በወንጀሉ አዲስ ክስ ይመሰረትበታል፡፡ ሆኖም ውሳኔው ሲሻር በዚሁ ምክንያት ውሳኔው የተሻረበት ሰው ሊደመጥ ይገባል፡፡[139] በመጥፎ ባህርይው ቀጥሏል ስለተባለ ብቻ በፈተና ጊዜ ላይ ያለው ሰው ቀርቦ ሳይደመጥ ቀደም ሲል በፍርድቤቱ የተሰጠው ነጻነት ተገፍፎ የእሥራት ቅጣቱን እንዲፈጽም ወደ ማረሚያቤት እንዲገባ መደረግ የለበትም፡፡ እንዲህ አይነቱ ውሳኔ የግለሰቦችን መሰረታዊ ነጻነት የሚጋፋ በመሆኑ[140] ፍርድቤቱ ገደቡን ሽሮ የእሥራት ቅጣቱ እንዲፈጸም ለማዘዝ ወንጀለኛውንና ገደቡ እንዲሻር አቤቱታ ያቀረበውን አካል አስቀርቦ ማከራከርና ገደቡን ለመሻር ምክንያት ሆኖ የቀረበው ነጥብ በማስረጃ የተረጋገጠ መሆኑን ማየቱ አስፈላጊ ነው፡፡ የኢፌዴሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 200 (2) "...ጥፋተኛው የሚያቀርበው ሃሳብ በቅድሚያ መሰማት አለበት" የሚል ሀረግ በግልጽ ቢያስቀምጥም ሃሳቡን ለማዳመጥ ፍርድቤቱ ሊከተል የሚገባው ሥነ-ሥርዓት ምን አይነት እንደሆነ እንደሌሎቹ ሃገሮች በግልጽ

137 የኢፌዴሪ የወንጀል ሕግ፣ አንቀጽ 200፡፡

138 ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 200(1)፡፡

139 ዚኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 200(2)፡፡

140 የኢፌዴሪ ሕገመንግስት፣ የኢትዮጵያ ፌዴደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሕገመንግስት፣ አዋጅ ቁጥር 1/1987፣ ፌዴደራል ነጋሪት ጋዜጣ፣1987፣ አንቀጽ 20፡፡

አላስቀመጠም፡፡[141] በአሜሪካ አንዳንድ ግዛቶች በተለይ የወንጀል ጥፋተኝነት ውሳኔ ገደብ ሲሻር ውሳኔው የሚሻርበት ወንጀለኛ ይህንኑ በተመለከተ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ በቅድሚያ እንዲደርሰውና በፍርድቤት ቀርቦ የቀረበበትን ምስክር እንዲጠይቅ እንዲሁም ተቃራኒ ማስረጃዎች አቅርቦ እንዲከላከል የሚደረግበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ይሆናል፡፡[142] ነገርግን በኢትዮጵያ የወንጀል ፍትህ አስተዳደር ሥርዓት ውስጥ የገደብ ውሳኔ መሻርን አስመልክቶ ግልጽ የሆነ ሕግና አሰራር ካለመኖሩም በላይ በአማራ ክልል ፍርድቤቶች እንዲህ አይነት ውሳኔ በብዛት እንደማይስተዋል ለዚህ ጥናት ዓላማ የተሰበሰቡ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡[143] በመሆኑም የወንጀል ቅጣት ውሳኔ ጊዜ መስጠትና ቅጣት እንዳይፈጸም ማገድን መሻር የሚመለከት የሥነ-ሥርዓት ክርክር በአማራ ክልል ፍርድቤቶች በተግባር ምን እንደሚመስል ለመገንዘብ መረጃ ባለመገኘቱ ተግባራዊ ችግሮችን ለመተንተን አዳጋች ሆኗል፡፡ ሆኖም በፈተና ጊዜ ላይ ያለ ሰው ሆነ ብሎ አዲስ ወንጀል ፈጽሞ በዚሁ ምክንያት ገደቡ እንዲሻርና ወደ ማረሚያቤት እንዲገባ ለፍርድቤት አቤቱታ ሲቀርብ አቤቱታውን የሚመለከተው ፍርድቤት ገደቡን ለመሻር ወንጀለኛው ፈጸመ በተባለው አዲስ ወንጀል ተከስሶ በፍርድቤት ጥፋተኛ እስካልተባለ ድረስ በዚሁ ምክንያት ገደቡ እንደማይሻር ከተደረገው ቃለ-መጠይቅ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡[144] በአጠቃላይ ሕጉ ለቅጣት ውሳኔ ጊዜ መስጠትና ቅጣት እንዳይፈጸም የማገድን ውሳኔ ለመሻር ውሳኔው ፍርደኛው መደመጥ እንዳለበት በመርህ ደረጃ ያስቀምጥ እንጅ ዝርዝር ሥነሥርዓቱን ለፍርድቤቶች ትርጉም የተወ ቢሆንም በአብዛኛው በአማራ ክልል ፍርድቤቶች ተግባራዊ ሲደረግ አይስተዋልም፡፡

---

[141] ዝኒ ከማሁ፡፡

[142] Joel Bassett, supra Note 66.

[143] በአማራ ክልል ከሚገኙ የወረዳና ከፍተኛ ፍርድቤት ዳኞች ጋር የተደረገ ቡድንተኮር ወይይት፣ 8/6/2011 ዓ.ም ተካበ አይነ ኩሉ፣ ይሄነው፣ጋሻው ሞላ፣ ሂዎት ታደሰ፣ ብርሃኑ አሰፋና ሌሎችም የምስራቅ ጎጃም፣ ሰሜን ሸዋ፣ ሰሜን ጎንደር፣ ሰሜን ወሎ እና ደቡብ ወሎ ከፍተኛና ወረዳ ፍርድቤት ዳኞች ጋር የተደረገ ቃለመጠይቅ፣ በየካቲትና በሚያዝያ ወር 2011 ዓ.ም፡፡

አቶ ኢብራሂም የሱፍ፣ ፕሬዝዳንት ምእራብ ጎንደር ዞን ከፍተኛ ፍርድቤት ፣ ስለገደብ መሻርና ተግባራዊ አፈጻጸሙን በተመለከተ የተደረገ ቃለመጠይቅ፣ መስከረም 3 ቀን 2012፡፡

[144] አቶ ፀጋየ ወርቅአየሁ፣ በአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድቤት የሰበር ሰሚ የስራ ሂደትና ችሎት ሰብሳቢ ዳኛ፣ የወንጀል ቅጣት ውሳኔ ገደብን መሻር አስመልክቶ የተደረገ ቃለመጠይቅ፣ ነሐሴ 16 ቀን 2011 ዓ.ም፡፡

" በደቡብ ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍርድቤት በዳኝነት ተሰይሜ ስሰራ ፖሊስ ከዚህ ቀደም በፈተና ጊዜ ላይ የነበረ ወንጀለኛን ወደችሎት ይዞ በመቅረብ አዲስ ወንጀል በመፈጸሙ ከዚህ ቀደም የተሰጠው ገደብ ተሽሮ ወደማረሚያቤት በመግባት ቅጣቱን ይፈጽም የሚል አቤቱታ አቀረበ፡፡ ዳኞች ጉዳዩን ስንመረምር ወንጀለኛው አሁን ፈጽሟል በተባለው ወንጀል ተከስሶ በክርክር ላይ መሆኑን በመገንዘብ ጥፋተኛ እስካልተባለ ድረስ ወንጀለኛ ነው፤ ብለን ከዚህ ቀደም የተሰጠውን የገደብ ውሳኔ በመሻር ቅጣቱን ይፈጽም ማለት የግለሰቡን ከፍርድ በፊት እንደንጹህ የመገመት ሕገመንግስታዊ መብት የሚጋፋ ነው፤ በማለት አቤቱታውን ውድቅ አድርገናል" በማለት ልምዳቸውን አካፍለዋል፡፡

አቶ ጌትየ አድማሴ፣ በአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድቤት የሰበር ሰሚ አጣሪ ችሎት ዳኛ፣ የወንጀል ቅጣት ውሳኔ ገደብን መሻር አስመልክቶ የተደረገ ቃለመጠይቅ፣ መስከረም 2 ቀን 2012 ዓ.ም፡፡

"በአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድቤት የይግባኝ ሰሚ ችሎት ዳኛ ሆኜ ስሰራ በፈተና ጊዜ ላይ የነበረ አንድ ፍርደኛ አዲስ ወንጀል በመፈጸሙ ገደቡ ተሽሮ ቀደም ሲል የተወሰነበትን የእስራ ቅጣት ጨምሮ እንዲፈጽም በስር ፍርድቤት ተወስኖበት በአቀረበው የይግባኝ ማመልከቻ `አዲሱ ወንጀል የተፈጸመው የፈተና ጊዜየን ከጨረስኩ በኋላ በመሆኑ የተገደበልኝን ቅጣት ከአዲሱ የወንጀል ቅጣት ጋር ተደምሮ እንድፈጽም መወሰኑ ተገቢ አይደለም`፤ በሚል አቤቱታ አቅርበው ስንመረምረው አዲሱ የወንጀል ድርጊት የተፈጸመው በተሰጠው የፈተና ጊዜ ውስጥ በመሆኑና ይሄው ጊዜ የሚሰላው የመጨረሻ ፍርድ ከተሰጠበት ጊዜ ጀምሮ እንጂ ቅጣት የተገደበበት ወንጀል ከተፈጸመበት ጊዜ ባለመሆኑ የስር ፍርድቤት የሰጠውን ገደብ በመሻር የእስራት ቅጣቱ ተጨምሮ እንዲፈጽም የተሰጠው ውሳኔ በሕግ መሰረት ስለሆነ ይግባኙ ውድቅ ተደርጓል" በማለት ሃሳባቸውን ገልጸዋል፡፡

## ማጠቃለያ

ለወንጀል ቅጣት ውሳኔ ጊዜ መስጠትና ቅጣት እንይፈጸም በመገደብ የፈተና ጊዜ ሰጥቶ የወንጀለኛውን አመል መፈተሽ በወንጀል ፍትህ አስተዳደር ሥርዓት ውስጥ ወንጀለኞችን ለማረም ከተዘረጉ አሰራሮች መካከል አንዱ በመሆን ያገለግላል፡፡ በወንጀል ክርክር የቀረበውን ክስና ማስረጃ መርምሮ ተከሳሹን በነጻ ማሰናበት አልያም የጥፋተኝነት ውሳኔ መስጠት የመደበኛ ክርክር አካል ነው፡፡ ወንጀለኛው በቀረበው ማስረጃ መሠረት ጥፋተኛ መሆኑ የተረጋገጠ እንደሆነ ፍርድቤቱ እንደነገሩ ሁኔታ ለቅጣት ውሳኔ ጊዜ ሊሰጥ እንደሚችል በኢፌዴሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 191 ሥር ተደንግጓል፡፡ የጥፋተኝነት ውሳኔ ካስተላለፈ በኋላ ቅጣትን አስመልክቶ በማከራከር ልዩ ልዩ የቅጣት ማክበጃና ማቅለያ ሁኔታዎችን ግምት ውስጥ በማስገባት ቅጣት ወስኖ አፈጻጸሙን በማገድ የፈተና ጊዜ መስጠት እንደዚሁ በአንቀጽ 192 ሥር ተመልክቷል፡፡

ለቅጣት ውሳኔ ጊዜ የሚሰጠው የወንጀለኛው ጠባይና ጥፋተኛ ሊባልበት የሚችለው የወንጀል ዓይነት ከሦስት ዓመት በማይበልጥ ቀላል እሥራት፣ በግዴታ ሥራ ወይም በመቀጮ ሊያስቀጣ የሚችል ሆኖ ሲገኝ ነው፡፡ ወንጀለኛው የጥፋተኝነት ውሳኔ ተወስኖበት ቅጣት ሳይወሰን ጊዜ ቢሰጠው አመሉን ሊያሻሽል ይችላል ተብሎ ከታመነበት ፍርድቤቱ አስፈላጊ ነው፤ የሚለውን ማስጠንቀቂያ በመስጠት ቅጣት የሚወሰንበትን ጊዜ ሊያዘገየው ይችላል፡፡ ይህ ማለት ወንጀለኛው በተሰጠው የፈተና ጊዜ የባህርይ መሻሻል ካመጣ ቅጣቱ ሳይወሰን ከመቅረቱም ባሻገር ፍርዱ እንዳልነበረ ተቆጥሮ የወንጀል ሪከርድ ሆኖ አይመዘገብም፡፡ ሆኖም የተሰጠው የፈተና ጊዜ መልካም ፍሬን ማስገኘት ያልቻለ እንደሆነ ገደቡ ተሽሮ ተገቢው ቅጣት ተወስኖ ወንጀለኛው እንዲፈጽም ይደረጋል፡፡ ይህ የገደብ ዓይነት በሕጉ በግልጽ ይደንገግ እንጅ በተለያዩ ምክንያቶች በኢትዮጵያ ወንጀል ፍትህ አስተዳደር ብቻ ሳይሆን እንደአሜሪካ ባሉ የዳበረ የፍትህ ሥርዓት ባላቸው አገሮችም በብዛት ሲተገበር አይስተዋልም፡፡ በአማራ ክልል ለቅጣት ውሳኔ ጊዜ መስጠት የተለመደ እንዳልሆነ የጥናቱ ግኝት ያሳያል፡፡

ለቅጣት ውሳኔ ጊዜ ከመስጠት ይልቅ ቅጣቱን ወስኖ አፈጻጸሙን ማገድ ይበልጥ ሥራ ላይ የሚውል የወንጀለኞች ማረሚያ መንገድ ነው፡፡ በወንጀል ፍትህ አስተዳደር ሥርዓት ወንጀለኛው ጥፋተኛ ተብሎ የእሥራት ቅጣት የተወሰነበት እንደሆነ ቅጣቱን ሊፈጽም ወደ ማረሚያቤት መላኩ የተለመደ ሆኖ ከእዚህ ይልቅ ቅጣቱ ተገድቦለት የፈተና ጊዜ ቢሰጠው ጠባዩን ሊያርም ይችላል ተብሎ ሲታመንበት ቅጣቱ እንዳይፈጸም ሊታገድ ይችላል፡፡ የቅጣት አፈጻጸምን ለማገድ በሕጉ የተመለከቱ መስፈርቶች መሟላት ይኖርባቸዋል፡፡ መስፈርቶቹም የወንጀለኛው አመል አንድ ጽኑ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶት ቢሞከር የሚሻሻል ከሆነና ወደፊት ወንጀል እንደማይፈጽም በፍርድቤቱ መታመኑ፣ ከዚህ ቀደም በጽኑ እሥራት ወይም ከሦስት ዓመት በሚበልጥ ቀላል እሥራት አለመቀጣቱና አሁን ጥፋተኛ በተባለበት ወንጀል ከአምስት ዓመት በሚበልጥ ጽኑ እሥራት የማይቀጣ መሆኑ ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡ እነዚህ መስፈርቶች ተሟልተው የተገኙ እንደሆነ ወንጀለኛው ቅጣቱ እንዲገደብለት ጥያቄ ሲያቀርብ ወይም በግልጽ ጥያቄው ባይቀርብም ፍርድቤቱ ካመነበት የቅጣት አፈጻጸሙ ሊታገድ ይችላል፡፡

የቅጣት ውሳኔው ወይም አፈጻጸሙ የታገደለት ወንጀለኛ ከሁለት እስከ አምስት ዓመት ሊደርስ የሚችል የፈተና ጊዜ ተሰጥቶት በክትትልና ቁጥጥር ሥር እንዲቆይ በማድረግ ባህርይው ሊፈተሽ ይገባል፡፡ ለዚሁም ተግባር ሊሰጡ የሚገባቸው የጠባይ አመራር ደንቦች

በሕጉ ተመልክተዋል፡፡ ለቅጣት ውሳኔ ጊዜ መስጠት ወይም አፈጻጸሙን በማገድ የፈተና ጊዜ የሚሰጠው ፍርድቤት በፍርዱ ወንጀለኛው በፈተና ጊዜ ሊከተላቸው የሚገቡትን የጠባይ አመራር ደንቦች ማመላከት ይጠበቅበታል፡፡ ይህ ከሆነ በፈተና ጊዜ ላይ ያለው ወንጀለኛ በተሰጠው የፈተና ጊዜ የጠባይ አመራር ደንቦችን ማክበርና አዲስ ወንጀል ከመፈጸም መቆጠብ ይኖርበታል፡፡ ይሁን እንጅ በአማራ ክልል ፍርድቤቶች ለወንጀል ቅጣት ውሳኔ ጊዜ መስጠትንና ቅጣት እንዳይፈጸም ከመገደብ ጋር ተያይዞ የሚስተዋሉ የአፈጻጸም ችግሮች አሉ፡፡ እነዚህም የፈተና ጊዜ እርዝማኔ በሕጉ ከሁለት እስከ አምስት ዓመት ሊደርስ እንደሚችል ይመላከት እንጅ የቅጣት መጠን፣ የወንጀል ክብደትና የወንጀለኛው ባህርይ ታሳቢ ሳይደረጉ በደምሳሳው የሁለት ዓመት ፈተና ጊዜ መሰጠቱ፣ የጠባይ አመራር ደንቦች በፍርድ መዝገቦች ላይ አለመገለጻቸው፣ አፈጻጸማቸውን ተከታትሎ ሪፖርት የሚያቀርብ ተቋም ወይም ባለሙያ አለመኖሩና ሌሎችም ናቸው፡፡ በእነዚህ ችግሮች የተነሳ በፍርድቤቶች የሚሰጠው የገደብ ውሳኔ መልካም ፍሬ ማስገኘቱን ለማረጋገጥ አስቸጋሪ ከመሆኑም በላይ ወንጀለኛውም ይሁን ማህበረሰቡ እንዲህ አይነቱን ውሳኔ እንደቅጣት አይቆጥሩትም፡፡ ይልቁንም ወንጀለኛው በነጻ እንደተለቀቀ በመቁጠር ለወንጀል ቅጣትና አፈጻጸም ገደብ ያለው ግምት የተሳሳተ እንዲሆን አድርጎታል፡፡

በፈተና ጊዜ እንዲቆይ የተደረገው ወንጀለኛ የጠባይ አመራር ደንቦችን ካከበረ ወይም ሌላ አዲስ ወንጀል በዚሁ ጊዜ ካልፈጸመ የተሰጠው ፈተና መልካም ፍሬ እንዳስገኘ ተቆጥሮ ወንጀለኛው መልካም ዜጋ ሆኖ መደበኛ ኑሮውን ይመራል፡፡ ይህም ማለት ፍርድቤቱ ለቅጣት ውሳኔ ጊዜ በመስጠት ወንጀለኛው በፈተና እንዲቆይ ወስኖ ከሆነ የጥፋተኝነት ውሳኔው እንዳልነበረ ከመቆጠሩም በላይ የወንጀል ሪከርድ ተደርጎ አይያዝበትም፡፡ ፍርድቤቱ ያገደው የቅጣት አፈጻጸምን ከሆነ ከፈተና ጊዜው መጠናቀቅ በኋላ ቅጣቱን እንዲፈጽም የማይደረግ ይሁን እንጅ በወንጀል ሪከርድነት ተመዝግቦ መቀመጡ አይቀሬ ነው፡፡ በተቃራኒው በተሰጠው የፈተና ጊዜ ውስጥ ወንጀለኛው በፍርዱ የተመለከተ የጠባይ አመራር ደንብ ካለ ይህንኑ ሳያከብር ወይም አዲስ ወንጀል ፈጽሞ ጥፋተኛ የተባለ እንደሆነ እንደነገሩ ሁኔታ ለወንጀለኛው ማስጠንቀቂያ ሊሰጠው ወይም የጠባይ አመራር ደንቡ ሊቀየር አልያም የፈተና ጊዜው ሊራዘም ወይም ገደቡ ሙሉ በሙሉ ተሽሮ ቅጣት ተወስኖ ወይም ተገድቦ የነበረው ቅጣት እንዲፈጸም ሊደረግ ይችላል፡፡ የፈተናው ጊዜ መልካም ፍሬ አላስገኘም ተብሎ የጸናው የገደብ ውሳኔ ሲሻሻል ወይም ሲሻር በፈተና ጊዜ የቆየውን ሰው ነጻነት ሊጋፋ ስለሚችል ወንጀለኛው የመደመጥ መብት እንደሚኖረው ሕጉ በመርህ ደረጃ ቢያስቀምጥም ዝርዝር የክርክር አመራር ሥነ-ሥርዓት አልተቀመጠለትም፡፡ በሕጉ የጠባይ አመራር ደንቦች ሳይከበሩ ወይም ወንጀል ተፈጽሞ ሲገኝ የተሰጠው የገደብ ውሳኔ እንደሚሻር ይመልከት እንጅ የጠባይ አመራር ደንቦች በአማራ ክልል ፍርድቤቶች በውሳኔ ላይ ባለመመልከታቸው ይሄው ሲፈጸም አይስተዋልም፡፡ አልፎ አልፎም ቢሆን የገደብ ውሳኔ ሲሻር የሚስተዋለው በፈተና ጊዜ ላይ ያለው ሰው አዲስ ወንጀል ፈጽሞ ጥፋተኛ እንደሆነ ሲወሰንበት ነው፡፡ ይህ በሚሆንበት ጊዜ ወንጀለኛው ታግዶለት የነበረውን ቅጣት ከአዲሱ ወንጀል ቅጣት ጋር ደምሮ እንዲፈጽመው ይገደዳል፡፡ በአጠቃላይ በዚህ ረገድ የኢትዮጵያ የወንጀል ሕግ ሲታይ ከውስን ክፍተቶች በቀር የተሟላና ዘመናዊ ቢመስልም በአሰራር የሚስተዋሉ ችግሮች ያሉ በመሆናቸው የአማራ ክልል ፍርድቤቶች ሕጉን ተግባራዊ በሚያደርጉበት ጊዜ ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡ በተለይም ፍርድቤቶች ለቅጣት ጊዜ መስጠት በሕጉ መሠረት ቢፈጸም ሊኖረው የሚችለውን ፋይዳ በማጤን ተግባራዊ የሚደረግበትን ሁኔታ ከግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርባቸዋል፡፡ በተጨማሪም የፈተና ጊዜ ሲሰጡ እርዝማኔውን ከወንጀሉ ክብድት፣ ከቅጣት መጠኑና ከወንጀለኛው ባሕርይ አንጻር መገምገም እንዲሁም

በፍርዱ ውስጥ ወንጀለኛው ሊከተላቸው የሚገቡ የጠባይ አመራር ደንቦችን ለይቶ በግልጽ ማስፈር መልካም ፍሬ ለማስገኘት የሚኖረውን ፋይዳ በመገንዘብ ለዚሁ ተገቢውን ትኩረት ሊሰጡ ይገባል፡፡ የክልሉ መንግስትም ወንጀለኛውን ለመከታተልና አስፈላጊውን መረጃ ለሚመለከተው አካል የሚያቀርብ፣ የተሰጡ የጠባይ አመራር ደንቦች በፈተና ጊዜ እንዲቆይ የተደረገው ወንጀለኛ በትክክል እያከበራቸው መሆኑንና ጥሰት ካለም ይህንኑ ሪፖርት የሚያደርግ እንዲሁም ሌሎች የወንጀል ቅጣት ገደብን ዓላማ ሊያሳኩ የሚችሉ ሥራዎችን የሚፈጽም አካል በማቋቋም በወንጀል ፍትህ ሥርዓቱ ውስጥ አማራጭ ሆኖ እያገለገለ ያለውን አሠራር እንዲበለጽግና ውጤታማ እንዲሆን ማገዝ ይኖርበታል፡፡

## Suspension of Penalty: The Legal Framework in Ethiopia and its Practice in the Amhara National Regional State Courts

*Belayneh Admasu* [*] *& Alemu Dagnew* [**]

### *Abstract*

*Conditional suspension of penalty is a legal device designed to suspend pronouncement and enforcement of penalty. Although the criminal proceeding presupposes conviction, sentencing and execution, articles 191 and 192 of the FDRE criminal code respectively provide for suspension of pronouncement and enforcement of penalty. Accordingly, a court may, upon the fulfillment of the conditions prescribed by this law, render either of the two depending on its possibility of reforming and reinstating the criminal.*

*Despite many challenges, suspending enforcement of penalty is commonly practiced in the regional courts. This study, therefore, attempted to identify the challenges thereto by employing a qualitative research method and arrived at the following major findings.*

*Unlike suspension of pronouncement of penalty, suspension of enforcement of penalty is rendered with the condition of two years' probation period regardless of severity of the crime, punishment and the conduct of the criminal. Besides, failure to state the rules of conduct in a judgments, absence of follow up mechanisms, nonexistence of independent probation entity/officer and procedural rule as to revoking suspension are the major pitfalls demanding urgent action in the criminal justice system.*

***Key words:*** Penalty, Suspension, Pronouncement, Enforcement, Probation, Rule of Conduct

[*] LLB (Addis Ababa University), LLM in criminal Law (Amsterdam University), Assistant professor of Law, Law school, Bahir Dar University. The author can be reached at badmaasu7@gmail.com or belaynehv@yahoo.com

[**] LLB (Jimma University), LLM in Criminal Justice and Human Rights Laws (Bahir Dar University), Assistant professor of Law, Law School, Bahir Dar University. The author can be reached at alemudag@gmail.com